

በኢሉባቦር ሀ/ስብከት በመቱ ት/ቤት የሠለጠኑ ካህናት ሲመረቁ

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

ዋጋው አንድ ብር

# ትንሣኤ



አዲስ አበባ ከተማ ግቢ ኪዳነ ምሕረት

ቁጥር ፵

መጋቢት ፲፱፻፸፯ ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »


አዘጋጅ
ልሣነወርቅ በዛብኅ ፤
ም/ ክንፈ ርግብ ማርቆስ




በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤


# ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ጉድጓዳችሁን ቆፍራችሁ ተጠባበቁ | ፪ |
| ቅዱስነታቸው በድርቅ የተጐዱትን ወገኖቻችንን ከመጐብኘት አያቋርጡም | ፬ |
| መስቀለ ክርስቶስ | ፭ |
| እግዚአብሔር በፍጥረቱ ደስ ይለዋል | ፯ |
| የመጨረሻው ተጠሪ | ፰ |
| የቤተ ሰብእ ዓምድ | ፱ |
| ዜና ሊቃውንት | ፲ |
| የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም | ፲፪ |
| ልማት በቤተ ክርስቲያን | ፲፬ |
| መድኃኔ ዓለም | ፲፮ |
| የጤና ዓምድ | ፲፰ |
| የግብርና በረከት | ፲፱ |
| እያስተማሩ መማር | ፳፩ |
| ሆሣዕና በአርያም | ፳፫ |
| ታማኙ አገልጋይ | ፳፬ |




ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ ፡-
አዲስ አበባ ፤

በቅድሚያ ከእግዚአብሔር አምላካችን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ፀጋና ሰላም ይብዛላችሁ እያልኩኝ በዚህች የመጀመሪያ ጽሑፌ ስተዋወቃችሁ መንፈሳዊ ደስታ ይሰማኛል ።

በየወሩ እየታተመ የሚወጣው ትንሣኤ መጽሔታችሁ መንፈሳዊ ዕውቀትን በመቸር (በመስጠት) በኩል የሚያበረክተው ክርስቲያናዊ አስተዋጽኦ አንባብያንን የሚያስደስት ነው ይኸው መጽሔታችሁ ቤተ ክርስቲያናችንን የሚያኮራት ነው ብል ማጋነን መስሎ አይታየኝም ፤ በተለይም ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በእትሞቹ ስለምታቀርቡ ወጣቱ ትውልድ ከአባቶቹ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣለትን እምነት እንዳይተውና ፈሩንም ስቶ ወደተለያዩ የሃይማኖት ድርጅቶች እንዳይገባና ትምህርተ ቤተ ክርስቲያንን በጽሑፍ አግኝቶ በማንበብ በመረዳት እንዲገለገል በማድረግ ረገድ የመጽሔቱ ጠቀሜታ የላቀ ነው ።

በአስደሳች ዝግጅታችሁ በኩል የምእመናን ትብብር ሳይለያችሁ ኃይልንና ብርታትን ቸሩ እግዚአብሔር ይሰጣችሁ ዘንድ ጸሎ ምኞቴ ነው ። እስኪ እኔም ለዛሬ ይህን ጅምር ግጥሜን ላበርክትላችሁ አእምሮን አዝናንቶ መንፈስን ያገለብታል ብላችሁ ካመናችሁበት እንዲታተም አድርጉልኝ ፤

ያቀረብኩት የግጥም መልእክት የሚያተኩረው በጾም ላይ ሲሆን በተለይም በአሁኑ ወቅት የጾምን ጥቅም ያልተረዱ አንዳንድ ሰዎች ስለሚገኙ በመጠኑ ለማስረዳት ነው ።

እጾማለሁ ።
እኔስ ዛሬ እጾማለሁ
የአምላክን ቃል አከብራለሁ ።
እጾማለሁ በጾም ወራት
ከጽድቅ ሥራ እንዳልራቆት ፤
ሙች እወድና በጾም ሥጋ
ነፍስን እንደ ጦር የሚወጋ ።
እኔስ ዛሬ እጾማለሁ
የአምላክን ቃል አከብራለሁ ።
አንተስ ወንድም አትጾምም ?
የአምላክን ቃል አታከብርም ?
አንችስ እህት አትጾሚም ?
ሕያው ቃሉን አትሰሚም ?
ኧረ እንጹም እባካችሁ
ጾምን መግደፉ ይቅርባችሁ ።
የመጣነው ከነቢያት
የወረደ ነው ከሐዋርያት
ደግሞም ከአበው ከቀደሙት ።
ልብ አድርገን ብናስተውል
ክርስቶስም አርባ ቀን ጹሟል ።
ፀጋ በረከት የሚገኘው
በጸሎትና በጾም ነው ።
እስኪ እባካችሁ ብሉይ አንብቡ
እየታገሳችሁ ከምግቡ ።
የጾም ታሪክን እንድትረዱ
ለልዑል እግዚአብሐር ስገዱ ።
ዳንኤል ከአንበሳ አፍ የዳነው
በጸሎትና በጾም ነው ።
ያ ታላቁ ነቢይ ዳንኤል
ባለትሩፋት ባለገድል ።
በጾም መሣሪያ ከአውሬ አፍ ድኗል ።
ጾም እኮ ናት ፈዋሺት
የሕይወት ቁስል መድኃኒት
ከዚህ በላይ ጠቀስኩ እንጂ ጥቂቱን
ለአብነት
ብዙ እኮ ነው የጾም ዋጋና ትሩፋት ።

ተማሪ ደርሰማ ትባ
ከቅ/ ማርያም የሰንበት ት/ቤት ተማሮች
ሸዋ ሀ/ ስብከት
ቡታጅራ

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ ፤

በቅድሚያ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር በሁላችን ላይ ይሁንልን ፤ ልዑል እግዚአብሔር ሰላምና ጤና ለግሶኝ በዚህች አጭር ጽሑፌ ከመንፈስ ቅዱስ ወንድሞቼና እህቶቼ ጋር ስተዋወቅ ከፍ ያለ የመንፈስ ደስታ ይሰማኛል ።

የትንሣኤን መጽሔት ማንበብ ከጀመርኩኝ እያሌ ዓመታት አልፈዋል በመጽሔቱም የሚዘጋጁት ትምህርቶች እጅግ በጣም ጠቃሚዎችና አስፈላጊዎች ናቸው በመጽሔቱ ላይ ከተለያዩ ግለሰቦች ጥያቄዎችና አስተያየቶች ይቀርቡበታል ፤ ከእናንተም የሚሰጡት መልሶች የሚያረኩና የመንፈስ ተሐድሶን የሚሰጡ ናቸው ።

በዚሁ ከቀጠላችሁ ይህ ዝግጅታችሁ ለተዋህዶ ሃይማኖታችን በበለጠ ለመስፋፋት.ስለሚያስችል ሥራችሁ በአምላክ ስም የተቃና ይሁንላችሁ በርቱ እያልኩ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቅርቤአለሁ ።

፩ኛ/ በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ዘወትር ከ፲፩ - ፲፪ ሰዓት የሚሰጠው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እጅግ በጣም ጥሩ መሆኑን እኔ ብቻ ሳልሆን ሁሉም እያደነቀው ነው ታዲያ ለምን በሌሎችስ አብያተ ክርስቲያናት በዚሁ ሰዓት የወንጌል ትምህርት እንዲሰጥ አይደረግም ? ችግሩ ምንድን ነው ? እባካችሁ ለሚመለከተው ክፍል አሳስቡልን ።

፪ኛ/ ቤተ ክርስቲያናችን ለምን ቋሚ የሆነ የዲያቆናትና የቀሳውስት ማሠልጠኛ ት/ቤቶች የሏትም ዓለሙ ሁሉ የሚቀናባት ያሬዳዊ ዜማችን ግዕዛዊ ቋንቋችን እንዳይረሳና ቤተ ክርስቲያናችን አገልጋይ አልባ እንዳትቀር ምን የታቀደ ዕቅድ አለ ? ይህ ሁኔታ መላውን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ሳያሳስብ እንደማይቀር ። እርግጠኛ ነኝ ስለዚህ ከሕዝበ ክርስቲያኑ ርዳታ ተጠይቆ የማሠልጠኛው ት/ቤት በቶሎ እንዲቋቋም በትንሣኤ መጽሔት መንፈሳዊ መልእክት እንድታስተላልፉ አደራ እላለሁ ።

ወደ ገጽ ፪ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# ጉድጓዶችን ቆፍራችሁ ተጠባበቁ

ጉድጓድን ቆፍሮ ውኃን ማጠራቀም ለጓሮ አትክልት ብቻ ሳይሆን ለመጠጥም ለአዝርእትም ያገለግላል። በቀድሞ ዘመን ነቢያት ይህንን በመገንዘብ ሰው ጉድጓድን ቆፍሮ እንዲጠቀም ያስተምሩ ነበር ። አንድ ጊዜ በእሥራኤል ሀገርና በአካባቢው ሁሉ ዝናም ጠፍቶ ነበር ዝናምም በመጥፋቱ ድርቅ ሆነና በሰውና በእንስሳ ላይ ከፍ ያለ እልቂት ሆነ የሚያሳዝን ረሀብ ከመሆኑም በላይ ተፈጥሮን የሚያስጠላ ችግር ተፈጠረ ።

ምንም እንኳ ለጊዜው ድርቅና ረሀብ ቢፈጠርም እግዚአብሔርን ጥግ ያደረገና ከእርሱም የተጠጋ ሰው ወድቆ ስለማይሰበር ቢወድቅም እንኳ ፈጥኖ እንደሚነሣ ስለሚታመን በዚያን ጊዜ የነበረው የይሁዳ መሪ ኢዮሳፍጥ በድርቁ ምክንያት የወረደውን እልቂት ተመልክቶ እኛስ በደለኞች ነን ግን እግዚአብሔርን ያላሳዘነ እግዚአብሔርን የሚጠይቅ ነቢይ በዚህ ቦታ አይገኝም ?

ሲል ጠየቀ ያን ጊዜ ነቢዩ ኤልሳዕን የሚያውቅ አንድ ሰው ሰማውና መኖርስ የኤልያስን እጅ ያስታጥብ የነበረ ኤልሳዕ የተባለ ነቢይ አለ አለው በዚህ ጊዜ የእሥራኤል መሪ የነበረው ኢዮራም የእግዚአብሔርን ህልውና ረስቶ በአምልኮ ጣዖት የነበረ ቢሆንና እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ባይችልም ከይሁዳ መሪ ከኢዮሳፍጥና ከሰማርያ መሪ ጋር ሆነው ወደ ነቢዩ ኤልሳዕ ሄዱ ሦስት መሪዎች ተያይዘው የሄዱትም ለሕዝቡ አዝነው ለወገኖቻቸው ተቆርቁረው ሳይሆን ፈረሶቻቸው ስላለቁባቸው ነው ።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት መሪዎች ምንም እንኳን አብረው ቢሄዱም ነቢዩ ኤልሳዕ ባያቸው ጊዜ የእሥራኤልንና የሰማርያን መሪዎች እናንተ ከእኔ ጋር ምን አላችሁና ነው ወደ እኔ የመጣችሁ ጣዖቶቻችሁን አትጠይቁምን ? ብሎ ከወቀሳቸው በኋላ ኢዮሳፍጥ ከእናንተ ጋር ባይኖርና እርሱን ባላፍር ኖሮ ባላየኋችሁም ነበር አሁን ግን የመጣችሁበትን አውቂዋለሁ ስለራሳችሁ ጉዳይ እንጂ ስለ ሌላም እንዳልመጣችሁ ተገንዝቤአለሁ ።

አሁን የነፋስን ድምፅ ሳትሰሙ የደመናንም መልክ ሳታዩ ዝናም ይዘንምላችኋል ነገር ግን ዝናሙ ሲዘንም በጎርፍ እንዳይሄድ ጉድጓዶችን ቆፍራችሁ ተጠባበቁ የቆፈራችሁት ጉድጓድ ይሞላላችኋል አላቸው እነሱም በኤልሳዕ ቃል አምነው ሂደው ጉድጓድ አስቆፍረው ሲጠባበቁ የነፋስ ድምፅ ሳይሰሙ የደመና ምልክትንም ሳያዩ ዝናም ዘንሞላቸው የቆፈሩትም ጉድጓድ ሞልቶላቸው ችግራቸው ሊወገድ ችሏል 2ኛ መ/ ነገሥት ፫ ፣ ፩-፳፯ የዚህ ዓይነት አጠቃቀም ዘዴ በዚያን ጊዜ ተወስኖ አልቀረም በየጊዜው ሲሠራበት ኑሯል ። ዛሬም ቢሆን በዚህ መጠቀም ይኖርብናል ።

እንግዲህ ጉድጓድን ቆፍሩ በዚሁም ተጠቀሙ የሚለውን ምክር በተግባር መተርጎም የእኛ ፋንታ ሊሆን ይገባል ። እኛ ጉድጓዱን ቆፍረን ከተጠባበቅን ቸርነት የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ እግዚአብሔርም ሐሳባችንን ለማሟላት ቅዱስ ፈቃዱ ይሆናል መቼም የሰው ልጅ ዓቅሙ በሚፈቅድለት መጠን በሥራ መድከም እንጂ ዝናሙን የሚያወርድ የተዘራውን የሚያበቅል የበቀለውንም ለፍሬ የሚያደርስ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን መዘንጋት የለብንም ።

ነቢዩ ኤልሳዕ የነፋስን ድምፅ ሳትሰሙ የደመናንም መልክ ሳታዩ ዝናም ይዘንምላችኋል ሲል መናገሩ ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ግንኙነት ስለ ነበረውና በጸሎቱ ከእርሱ ጋር ተነጋግሮ የሚሆነውን ነገር ስለሚያውቅ ነው እንጂ እንዲሁ በከንቱ አፉ እንዳመጣ የተናገረው አይደለም ።

ስለዚህ እኛም ከላይ እንደተነገረው የቆፈርነውን ጉድጓድ ዝናመ ምሕረቱን አዝንሞ እንዲሞላልን እግዚአብሔር አምላካችንን እንለምነው ለምኑ ይሰጣችኋል ፈልጉ ታገኛላችሁ ተብሎ ተጽፏልና ።



# ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

፫ኛ/ ከትምህርትም ሆነ ከሥራ ዓለም ተለይተን ያለ አንድ ሥራ የተቀመጥን ብዙ ክርስቲያኖች ስላለን በቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር ተሰብስበን የግዕዝ የቅዳሴ የወንጌል ትምህርት እንድንማር ቢደረግልን ምን ችግር የሚፈጥር ይመስላችኋል?የሚመለከተውንክፍልአነጋግራችሁ መልሱን በትንሣኤ መጽሔት አውጡልኝ ።

የመጽሔቱ ተከታታይ
ተማሪ ሙላቷ ዓለሙ
አ.አ. ከተማ

መልስ ፤

ተማሪ ሙላቷ የመጽሔታችን ተከታታይ በመሆን ስላቀረብሽልን ምስጋና እኛም በበኩላችን መንፈሳዊ ሰላምታችን በማቅረብ ላቀረብሽልን ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን ።

ሀ. ከ፲፩ - ፲፪ ሰዓት የሚሰጠው መንፈሳዊ ትምህርት መንፈሳዊ ትምህርት ለሚፈልጉ አመችና አስደሳችመሆኑ አይጠረጠርም ይህም በመሆኑ በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያንና በመሳሰሉትም አብያተ ክርስቲያን በሳምንት ሁለት ቀን ቅዳሜና እሁድ በተጠቀሰው ሰዓት ከ፲፩ - ፲፪ ትምህርተ ወንጌል ይሰጣል በሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ለመማር ፈቃደኞች የሆኑ ክርስቲያኖች ካሉ ለማስተማር የተዘጋጁ መምህራን በብዛት ስላሉ የአስተማሪ ችግር የለም በእውነት የእግዚአብሔርን ቃል ለመማርና ለማወቅ የሚፈልጉ ምእመናን የዕረፍት ጊዜያቸውን በቦዘን ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ተገኝተው ጸሎት

በመጸለይ ትምህርተ ወንጌልን በመስማት ቢያሳልፉት መልካም ነው ።

ሁለተኛው ጥያቄ ቤተ ክርስቲያናችን ለምን ቀዋሚ የሆኑ የዲያቆናትና የቀሳውስትማሠልጠኛዎችየሏትም?ያሬዳዊ ዜማችንና ግዕዛዊ ቋንቋችን እንዳይረሱ ት/ ቤቶች ይኑሯት የሚል ነው ። ተማሪ ሙላቷ ዓለሙ በየአህጉረ ስብከት ተዘዋውረሽ የአልተመለከትሽ ስለሆንሽ ይሆናል እንጂ ቤተ ክርስቲያናችን ብዙ የዲያቆናትና የቀሳውስት ማሠልጠኛ አሏት የግዕዝና የዜማ ትምህርት ቤቶችም በብዛት የሚገኙባቸው አህጉረ ስብከት ይገኛሉ (ከእነርሱም ጎንደርና ጎጃም ትግራይ ለማስረጃ የሚጠቀሱ ናቸው) በእነዚህ አህጉረ ስብከትና በመሳሰሉትም የሚማሩት ዲያቆናትና ቀሳውስት ዜማና ቅኔ አዋቂዎች መምህራን እየሆኑ ሌላውን ስለሚያስተምሩ አህጉረ ስብከቱ ማሠልጠኛዎች ሊባሉ የሚበቁ ናቸው በሌላም በኩል ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ ፲ ማሠልጠኛዎችና አንድ ከፍተኛ መ/ ትምህርት ቤት አላት ያሬዳዊ ዜማችን ግዕዛዊ ቋንቋችን በሚገባ ተጠብቆ ይኖራል ዲያቆናትምቀሳውስትም ይሠለጥናሉ የዲያቆናትና የቀሳውስት ማሰልጠኞች የተጠቀሱት አህጉረ ስብከት ናቸውና ተማሪ ሙላቷ በሦስተኛው ጥያቄሽ ላይ በቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር ተሰብስበን የግዕዝ የቅዳሴ የወንጌል ትምህርት እንድንማር ቢደረግልን ምን ችግር የሚፈጥር ይመስላችኋል ? የሚመለከተውን ክፍል አነጋግራችሁ መልሱን በትንሣኤ መጽሔት አሳትማችሁ አውጡልኝ የሚል ነው ።

የሚማር ከተገኘ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ለማስተማር የተቀጠሩ መምህራን ስለሚገኙ ወደ እነርሱ እየሄዱ የግዕዝም ሆነ የቅዳሴ የትርጓሜ ወንጌልንም ሆነ ሌላ መንፈሳዊ ትምህርት ለመማር ይቻላል ስለዚህ ተማሪ ሙላቷ ዓለሙ ለመማር ፍላጐት ካለሽ የአስተማሪ ችግር ስለሌለ ወደ ፈለግሽው ቤተ ክርስቲያን ሄደሽ ለመማር ትችያለሽ ።

# ታማኙ አገልጋይ

ከገጽ ፳፱ የዞረ

በማብሠርና በመዝራት የኖሩ ጠቢባን በትንሣኤ ዘጉባኤ ጊዜ ክብራቸው እንደ አጥቢያ ኮከብ ይደምቃል ብዞቹንም ወደ ጽድቅ የመለሱ ይላል ዳንኤል ም. ፲፪ ቁ.፫ ።

ሰነፍ የተባለው ተምሮ ሳያስተምር ኃላፊነቱን ዘንግቶ ሳይወጣ ሳይወርድ ጊዜውን እየተሳለቀ ያሳለፈ ነው ። የተጻፈው ሁሉ እኛ ልንማርበትና ልንገስፅበት ነው የተጻፈው ብሎ መጽሐፍ እንደተናገረው እኛም ኃላፊነትን ወስደን በመጀመሪያ መምህሮቻችን በማድከም ምረን ባናስተምርና ባለን ኃላፊነትበትክክል ባንሠራበት የሰነፉ አገልጋይ ምሳሌ ይፈጸምብናል ። ተግተን ብንሠራ ግን ባለ ቤቱ ለትጉሆን ሠራተኞች የሰጠውን ዋጋ በደብረ ጽዮን ይሰጠናል ስለዚህ በትጋትና በንቃት ሠርተን ዋጋችንን ከእግዚአብሔር ለማግኘት ያብቃን ።

ቄስ ገብረ መስቀል ቸኮል



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስነታቸው በድርቅ የተጐዱትን ወገኖቻችን ከመጐብኘት አያቋርጡም

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በድረቅ ምክንያት ችግር የደረሰባቸውን ወገኖ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በድርቅ የተጐዱትን ወገኖች ሲያጽናኑ

ቻችን ከመርዳትና ከመጐብኘት አቋርጠው አያውቁም ባለፈው ጥር ወር በትግራይ ሀ/ ስብከት በመቀሌ አካባቢ የሚገኙትን ችግረኞች ወገኖቻችን እየተዘዋወሩ ከጐበኙ በኋላ ለችግረኞች መርጃ የሚሆን ፳፩ ሺህ ብር ለርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ሰጥተዋል ። ይህን ገንዘብ ከአሁን በፊት በቅዱስነታቸው ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖቻችን መርጃ ከተሰጠው ፪፻፳፫ሺህ ሁለት መቶ ሃያ አምስት ሺህ ብር በተጨማሪ የተሰጠ ሲሆን ችግሩ እስከሚወገድ ድረስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በሚቻላት ሁሉ ችግረኞችን ለመርዳት ጥረት እንደምታደርግና ችግሩ በጣም አሳሳቢ ስለሆነ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በገንዘብም ሆነ በጉልበት ሊረባረብበት እንደሚገባ ቅዱስነታቸው አሳስበዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በመቀሌ ጉብኝታቸው የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ. የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ በቅርቡ ተቀብሎ ከሚንከባከባቸው በድርቁ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ፲፻፶ ሕፃናት መካከል በመቀሌ የሕፃናት ማሳደጊያ አዳሪ ቤት ፫፻፶ ሕፃናትን እንዲሁም በጎጃም ሀ/ ስብከት በባሕር ዳር አውራጃ በሚገኘው የሕፃናት ማሳደጊያ አዳሪ ቤት ፩፻፶ ሕፃናትንና ተጨማሪ ፭፻ የሙታን ልጆችን ለመቀበል ሥራው በመጣደፍ ላይ ያለውን ቤት ጐብኝተው ሌላ ተጨማሪ የሕፃናት ማሳደጊያ ቤት በአስቸኳይ እንዲጀመር አባታዊ መመሪያ ሰጥተዋል ።

በዚህ ጉብኝታቸው ብፁዕ አቡነ ገሪማ በምድረ ሱዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሊቀ ጳጳስና የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተ/ዋና ጸሐፊ ነበሩ ቅዱስነታቸው በሁለቱም አህጉረ ስብከት ሲደርሱ የየአህጉረ ስብከቱ ሊቃነ ጳጳሳትና ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

እንዲሁም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በኤርትራ ሀ/ ስብከት በአሥመራ በአቆርዳትና በምጽዋ አውራጃዎች አካባቢ የሚገኙትን የችግረኞች ወገኖቻችን መጠለያዎች እየተዘዋወሩ ከጐበኙ በኋላ ለችግረኞች መርጃ የሚሆን ፺ሺህ ብር ለግሠዋል ይህም ገንዘብ ከአሁን ቀደም በቅዱስነታቸው ለችግረኞች ከተሰጠው ሌላ በተጨማሪ መጠለያ ለማሠራት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በዝግጅት ላይ መሆኗንና ወደ ፊትም አቅሟ በሚፈቅደው መጠን ርዳታ ከማድረግ እንደማትቆጠብ ቅዱስነታቸው በጉብኝታቸው ወቅት አስረድተዋል ።

ቅዱስነታቸው በድርቅ የተጐዱትን የመጠለያ ጣቢያዎችና የዕጓለ ማውታ ሕፃናት አዳሪ ቤቶች ከመጐብኘታቸውም ሌላ በምጽዋና በአቆርዳት የሚገኙትን የርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን የሠርቶ ማሳያ ጣቢያዎችንና ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን እየተዘዋወሩ ተመልክተዋል በጉብኝቱም ወቅት ፡-

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ የኤርትራ ሀ/ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ፤

ብፁዕ አቡነ ኤልያስ በጅቡቲ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ፣ብፁዕ አቡነ ገሪማ በምድረ ሱዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስና የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተ/ዋና ጸሐፊ የተገኙ ሲሆኑ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና የመጠለያዎች ሐላፊዎች አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ከዚህም ሌላ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት የተላከው ግምቱ ፳ሺህ አምስት ሺህ የሆነ ርዳታ የያዘው ከሆላንድ የመጣው ዲሲ ፲ ማርቲን አኤሮፕላን ቦሌ አየር ማረፊያ ሲደርስ ልዩ ልዩ ርዳታዎችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛው ተረክበዋል ።

ይህም ርዳታ ቤተ ክርስቲያኒቱ ላቀደችው ፲፺ የመጠለያ ጣቢያዎች የሚውል ሲሆን አራት የገጠር መኪናዎችን ፴ሺህ ብርድልብስ አያሌ ድንኳኖችንና የምግብ ዕቃዎችን የሚያጠቃልል ነው ይህንንም ርዳታ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ እየተዘዋወሩ አንድ በአንድ ተመልክተዋል ።

# መስቀለ ክርስቶስ

መስቀል ቀድሞ ከአሪት ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ድረስ ከፍተኛ የሆነ ወንጀል የሠራ ሰው በመንግሥት ትእዛዝና ፍርድ ተሰቅሎ የሚሞትበት ነው ።

በዚህ ሁኔታ ብዙ ዘመን ሲሠራበት ከቆየ በኋላ ዓመተ ዓለም አልፎ ዓመተ ምሕረት በተተካ በ፴፫ ዓ.ም. መጋቢት ፳፯ ቀን በዕለተ ዓርብ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አይሁድ በሐሰትና በቅንዓት ተነሥተው በሐሰት በመመስከርና በመፍረድ በመስቀል ላይ ሰቅለው በአምስት ምስማሮች ቸንክረውታል ፤ በመስቀል ላይ የፈሰሰው ደሙም የዓለምን በደልና ኃጢአት አጥፍቷል ፤ ክርስቶስ ሞቶ ተቀብሮ በሦስተኛው ቀን ከተነሣ በኋላ ተሰቅሎበት የነበረው የእንጨት መስቀል እንደ ዕንቁ እያበራ ከመታየቱም በላይ አጋንንትን ሲያስጮህና ሲያባርር የታመመ ሲያድን ሙት ሲያነሣ አይሁድ ተመልክተው ምቀኝነትና ቅንዓት ስላያዛቸው ጥልቅ የሆነ ጉድጓድ ቆፍረው በመቀበር የቤት ጥራጊና የቆሻሻ መጠራቀሚያ እንዲሆን ወሰኑ ።

ከአንደኛው መቶ ዘመን ጀምሮ እስከ አራተኛው መቶ ዘመን ድረስ የተከማቸው ቆሻሻ እንደ ተራራ ሆኖ ይታይ ነበር ይባላል ። በ፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ የእሌኒ ንግሥት ልጅ ታላቁ ቈስጠንጢኖስ በቁስጥንጥንያ በነገሠ ጊዜ መክስምያኖስና ዲዮቅልጥያኖስ የሚባሉ አላውያን ነገሥታት ነግሠው በክርስቶስ ያመኑትን ክርስቲያኖች ሁሉ ያሬዱና ያሳድዱ ነበር ።

ቆስጠንጢኖስም ምንም እንኳን ገና ያልተጠመቀና በክርስቶስ ያለመነ ቢሆንም የክርስቲያኖች በግፍ ማለቅና መሰቃየት ስለአሳዘነው እነርሱን ለመርዳት ቆርጦ ተነሣ የእግዚአብሔር ኃይልና ርዳታም ከርሱ ጋር ሁኖ የብርሃን መስቀል በፀፍፀፈ ሰማይ ላይ ተቀርፆ ታየው ።

ከዚህም አያይዞ መልአኩ ኡራኤል ተገልጾ ቈስጠንጢኖስ ሆይ በዚህ ባየኸው ትምእርተ መስቀል ምልክት የውጩንም የግቢውንም ረቂቅና ግዙፍ ጠላትህን ሁሉ ታቸንፍበታለህ ብሎ ነግሮት ከፊቱ ተሠወረ ።

ንጉሡ ቆስጠንጢኖስም ይህን ታላቅ ምሥጢር እንደተረዳ መስቀሉን በልብሰ መንግሥቱና በሠራዊቱ መለዮ ልብስ ላይ እያስቀረፀና እያስጠለፈ ሙሉ ዝግጅት ካደረገ በኋላ የክርስቲያን ጠላት በሆነው በሮም ላይ በነገሠው በመክስምያኖስ ላይ ዘምቶ ንጉሡን ድል አድርጐ ክርስቲያኖችን ነፃነት አውጥቶ የተሰደዱት ክርስቲያኖች ሁሉ ወደ የሀገራቸው ተመልሰው በነፃነት እንዲኖሩ ሲል ሚላኖ በተባለች ከተማ ላይ አዋጅ አስነገረ ጥቂት ቆይቶ የክርስቲያን ሃይማኖት ደስ ስለአሰኘው በክርስቶስ ስም አምኖ ተጠመቀ ።

የቆስጠንጢኖስ እናት እሌኒ ንግሥትም ልጇ ቆስጠንጢኖስ በክርስቲያን ሃይማኖት አምኖ የተጠመቀልኝ እንደሁ ወደኢየሩሳሌም ሄጄ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሎበት የነበረውን ክቡር መስቀል ከተቀበረበት አስቆፍሬ አውጥቼ ቤተ መቅደስ በወርቅ በዕንቁ አሠርቼ በክብር በማስቀመጥ እንዲቀደስበትና እንዲጸለይበት አደርጋለሁ ብላ ለፈጣሪዋ ተስላ ነበርና ስዕለቷስለተፈጸመላትከልዩልዩስጦታ ናዝግጅትጋርብዙሠራዊትአስከትላ ከቁስጥንጥንያ ተንሥቶ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደች ከዚያም ክቡር መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ለማወቅ ብዙ ችግር ገጥሞአት ነበር ። ብዙ ዓመታት የሆናቸውን ሽማግሌዎችን በመጠየቅ እነ ኪራኮስን አግኝታ የመስቀሉን ቦታ ጠይቃ ቸዋለች እነርሱም ንግሥት ሆይ አይሁድ መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ሕዝ





www.ethiopianorthodox.org

ብ እንዲያውቀው ብለው በአዋጅ የቆሻሻ መጣያና መከማቻ እንዲሆን ስለአደረጉት ከቆሻሻው ብዛት የተነሣ እንደ ተራራ ሁኖአል ፤ የቀደሙት አባቶቻችን የተቀበረው ከዚህ ላይ ነው ሲሉ ሰምተናል ፤ ብለው ቦታውን አመለከቷት እሌኒ ንግሥትም ወደተነገራት ቦታ ሄዳ መሬቱን በመመርመር ላይ እንዳለች መልአኩ ኡራኤል ተገልጾ በዚህ ቦታ ላይ ሰባት ቀን ምህላ ካስደረግሽ በኋላ ነው የሚገለጽልሽ አላት ።

እርሷም እንደተነገራት ሰባት ቀን በምህላ ከሰነበተች በኋላ ዳግመኛ መልአኩኡራኤል ተገልጾየመስቀሉን ልዩ መቃብር ለይተሽ የምታውቂው ደመራአስደምረሽ በእሳትአቀጣጥሊው በዚያ ላይ ነጭ ዕጣን ጨምሪበት የደመራው ጢስ ወደሰማይ ወጥቶ ተመልሶ መስቀሉ ከተቀበረበት ላይ ይሰግዳል በዚያ ምልክት መስቀሉን አስቆፍረሽ ለማውጣት ትችያለሽ ብሎአት ተሠወረ ።

እሌኒ ንግሥት ይህን ምሥጢር ለገለጸላት ለእግዚአብሔር ጥልቅ ምስጋና አቅርባ መስከረም ፲፮ ቀን በጐልጐታ ላይ ከፍተኛ የሆነ ደመራ አስደምራ ምህላ ከተደረገ በኋላ በእሳት እንዲቀጣጠል አድርጋ በነደደው ደመራ ላይ ዕጣን አስጨመረችበት ፤ የዕጣኑ ጢስ ወደሰማይ ወጥቶ እንደገና ተመልሶ መስቀሉ ከተቀበረበት ቦታ ላይ እንደ ቀስተ ደመና ሲሆን አየች ።

እሌኒ ንግሥትም ይህን ምልክትካገኘች በኋላ በገንዘቧ ብዙ ሠራተኞችን ቀጥራ ቁፈራውን መስከረም አስራ ሰባት ቀን አስጀምራ መጋቢት አስር ቀን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሎበት የነበረው ክቡር መስቀል ብርሃን ተጐናጽፎ ተገኘ እሌኒ ንግሥትም ፈጣሪዋ ልፋቷንና ድካሟን ተመልክቶ የተሰቀለበትን መስቀል ለማግኘት ስለአስቻላት ከፍ ያለ ምስጋና ለእግዚአብሔር አቀረበች ለመስቀሉም ሰገደች ለመስቀሉም ክብር ስትል ልዩ ልዩ ዝግጅት አድርጋ ወደጐልጐታ በሰልፍና በዝማሬ ስታጉዝ አጋንንት ያደሩባቸው ሕሙማን ተፈውሰዋል ፤ ሙታን ተነሥተዋል ።

ልጅዋ ቆስጠንጢኖስም ለክብረ መስቀሉ ሰባት ቀን በዓል አደረገ ከዚያም በኋላ እሌኒ ንግሥት ታላቅ ቤተ መቅደስ ጐልጐታ ላይ አሠርታ መስከረም አስራ ስድስት ቀን ቅዳሴ ቤቱን አከበረች ፤ ስለዚህ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ቁፋሮ የተጀመረበትን መስከረም ፲፯ ቀን መስቀሉ የተገኘበትን መጋቢት አሥር ቀን በየዓመቱ ታከብራለች ፤

አባ ገብረመስቀል ተስፋዬ ዘገነተ ማርያም ።

# በምዕራብ ሀገሮች የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አባላት የተወጣጣው ፺፩ ዶላርና ፬፻፶፬ የእንግሊዝ ፓውንድ ተላከ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጥቅምት ፲፪ ቀን ፲፱፻፸፯ ተሰብስቦ በሀገራችን ላይ በደረሰው ድርቅ ምክንያት የተጐዱትን ወገኖቻችን ለመርዳት ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የአንድ ወር ደመወዙን እንዲሰጥ ሲል በውሳኔ ማስተላለፉ የሚታወስ ነው ።

ቅዱስ ሲኖዶስ ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት በምዕራብ ሀገሮች የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባላት ፺፩ሺ.፬፻፵፰.፳፫. ዶላር ዘጠና አንድ ሺህ አራት መቶ አርባ ስምንት የአሜሪካ ዶላር ከሃያ ሦስት ሳንቲም እንዲሁም ፬፻፶፬ አራት መቶ ሃምሳ አራት የእንግሊዝ ፓውንድ አዋጥተው የካናዳ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ በሆኑት ሊቀ ካህናት ምሳሌ ዕንግዳና በትሪንዳድና ቱቤጐ ቤተ ክርስቲያናችን ዋና ጸሐፊና ረዳት ቄስ ተክለ ማርያም ጣሪን እጅ ተልኳል ።

ይህንንም የተውጣጣውን ገንዘብ በልዑካኑ እጅ የላኩት ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ሊቀ ጳጳስ በምዕራብ ሀገሮችየኢትዮጵያኦርቶዶክስተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናቸው ልዑካኑ መልእክተኞቹ የተላከውን ገንዘብ ለቅዱስነታቸው ባስረከቡበት ወቅት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው እንዲሁም የመምሪያ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

ቅዱስነታቸው በምዕራብ ሀገሮች የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባላት ስለአደረጉት አስተዋጽኦ አመስግነው የተላከውም ገንዘብ ለችግረኞች ወገኖቻችን በቶሎ እንደሚደርስ ቅዱስነታቸው በተጨማሪ ገልጸውላቸዋል ።



# እግዚአብሔር በፍጥረቱ ደስ ይለዋል ።
## መዝሙር ፻፫.፴፩

እግዚአብሔር አምላክ ከዕለተ እሁድ ጀምሮ እስከ ዕለተ ዓርብ የፈጠራቸው ፍጥረታት እጅግ በጣም ብዙዎች ናቸው የስነ ፍጥረት ሊቃውንት እንደሚናገሩት ብዙውን አንድ ብዙውን አንድ እያሉ ቢቆጥሩ ፳፪ ይሆናሉ ፤ ከ፳፪ቱም ፍጥረታት አንዱ የሰው ልጅ ነው ።

ፍጥረታትን ከፈጠረ በኋላ ሰውን በአርአያውና በምሳሌው ፈጥሮ ሲያበቃ ወስዶ በምድረ ገነት አስቀምጦታል ፤ በምድረ ገነትም ሳለ ከሰማይ በታች ከምድር በላይ በሚገኙ ፍጥረታት እንዲጠቀምባቸው ሲፈቅድለት በገነት ከሚገኙ ዕፀዋት መካከል የአንዷን ፍሬ እንዳይበላ ከልክሎት ነበር ።

ስለዚህም እንስሳትና አራዊት ወደ እርሱ እየመጡ አልበህ ጠጣን አርድህ ብላን ይሉት ነበር ፤ እርሱም እግዚአብሔር አምላክ ምን አሳጥቶኝ ከምድር በላይ ከሰማይ በታች ያለውን ሁሉ ሰጥቶኛል እናንተንስ በዚያው ባላችሁበት ያርባችሁ ያስባችሁ በማለት እየመረቀ ያሰናብታቸው ነበር ዘፍ.፪.፲፱ ።

አዳምና ሔዋን የፈጣሪያቸውን ትእዛዝ ጠብቀው በገነት በተድላ በደስታ የኖሩት ከሰባት ዓመታት አይበልጥም መጽሐፈ ኩፋሌ ምዕ. ቁጥር

በገነት የኖሩትም በሥራ ፈትነት ሳይሆን በዚያው የሚገኙትን አትክልት እየኮተኮቱና እያበጁ ነበር ፤ ነገር ግን ሰይጣን በኑሮአቸው ቀናባቸውና በሥጋ ከይሴ ተሰውሮ ሂዶ እግዚአብሔር አምላክ እንዳይበሏት የከለከላቸውን የእንጨት ፍሬ ቀጥፈው ቢመገቡ ካላቸው ክብር የበለጠ ክብር እንደሚያገኙ ነገራቸው እነርሱም እውነት ስለመሰላቸው እንዳይመገቡ እግዚአብሔር የከለከላቸውን የዕንጨት ፍሬ በሉ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ የሞት ሞትን ፈረደባቸው እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ እነርሱንም ያሳተው ከይሴ ተረገመና በልቡ እየተሳበ ፀበለ መሬት እየላሰ እንዲኖር ሆነ ።

በአዳምና በሔዋን ምክንያት ምድርም ተረገመች አዳምና ሔዋን ትእዛዘ እግዚአብሔርን ሳያፈርሱ የሚጣፍጡ ፍሬዎችን የተስተካከሉና የለሰለሱ ዛፎችን ታበቅል የነበረችው ምድርም ስለተረገመች እሾህንና አሜከላን አበቀለች ዘፍ. ፪.፲፯

ቃኤል በወንድሙ በአቤል ላይ በጠላትነት ተነሥቶ በገደለው ጊዜ ምድርን ባረስካት ጊዜ ኃይሏንም ደግሞ አትሰጥህም በምድር ላይ ተቅበዝባዥና ኮብላይም ትሆናለህ አለው ይህም የሰው ልጅ በወንድሙ ላይ የማይገባ ሥራ ሲሠራ ሥራው ሁሉ የማይባረክለት መሆኑን ያስረዳናል ። ዘፍ. ፬.፲፪

ኖኅ ቤተሰቦቹ ጋር ከጥፋት ውሀ ከዳነ በኋላ መሥዋዕት በመሰዋት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ቢጠይቅ እግዚአብሔር ተገልጦ ለኖኅ እንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ ቢበድል በውሃ አላጠፋውም የሰው የልቡ አሳብ ክፉ ነውና ከታናሽነቱ ጀምሮ ደግሞም ሕያውን ነፍስ ሁሉ አላጠፋምከአሁን ቀደም እንዳጠፋሁ በምድር ዘመን ሁሉ መዝራት ማጨድና ብርድ ትኩሳትም በጋ ክረምትም ሌሊትና ቀንም አያርፍም ሲል ነግሮታል ኦሪ.ዘፍ. ፰.፳፩

ይህ ሁሉ የሚያስረዳን የሰው ልጆች ከሚሠሩት በደልና ሕግ አፍራሽነት የተነሣ በተለያዩ መንገዶች ወደ ሰዎች የሚታዘዙትን የችግር ምንጮች ነው ፤ እሾህና አሜከላ በአዳምና በሔዋን ስሕተት እንደበቀሉ ስንመለከት በኖኅ ዘመን በነበሩት ሰዎች በደል ምክንያት ደግሞ የሰው ልጅ እድሜ ማጠርና ብርድና ትኩሳት እንደተጀመሩ ለመረዳት እንችላለን ።

እንዲሁም በሙሴ ዘመን ፈርዖን ሕዝበ እስራኤልን በነፃ አሰናብቶ እንዲሰዳቸው እግዚአብሔር ሙሴን ቢልክበት እግዚአብሔርን አላውቅም እስራኤልን ባሮቼንም አልለቅም በማለቱ አሥር የተለያዩ መቅሠፍቶችን ልኮ አሁንም በመጨረሻ በስጥመት እንደ ቀጣው ከታሪክ ለመረዳት እንችላለን ።

በሚሠራው ሥራ የማይደሰት ሰው አይገኝም ቢከፋም ቢበጅም ሥራ ለሠራው ያስደስታል እግዚአብሔር አምላክም በሥራው ደስ እንደሚለው በርእሱ ተገልጾአል ። እኛ ሁላችንም የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች መሆናችንን እና ምናለን እርሱ ፈጠረን እንጂ እኛ በእኛ አልተፈጠርንም ተብሎ እንደተነገረው የተፈጠርነው በእግዚአብሔር ቸርነት ስለሆነ የምንሠራው መልካም ሥራ አምላካችን የሚያስደስተው ሲሆን ክፉ ሥራችን ደግሞ በጣም ያሳዝነዋል ቅዱስ መጽሐፍ እግዚአብሔር አምላክ ሰውን በመፍጠሩ አዘነ ሲል እናገኘዋለን ።

መልካምና የተወደደ ሥራ ሠርተን ፈጣሪያችን ማስደሰት እንጂ የማይገባ ሥራ በመሥራትና ትእዛዙን በማፍረስ አምላካችን እንዲያዝን ማድረግ አይገባንም ።

የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እኛ ጠብቀን ስንራመድ እኛን ለማገልገል የተፈጠሩትም ፍጥረታት ለእኛ ይታዘዙልናል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ጥር ፳፩ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. አዲስ አበባ በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም በዓሉን ለማክበር ለተሰበሰቡት ምእመናን ጸሎተ ምዕዳን ሲያደርጉ ባስተላለፉት መንፈሳዊ መልእክት ላይ “እግዚአብሔር የፈጠራቸው ፍጥረታት ብዙ ናቸው ነገር ግን ከፍጥረታቱ መካከል ሰውን በአርአያውና በምሳሌው ፈጥሮ በዝናብ አብቅሎ በፀሐይ አብስሎ በነፋስ አሳ



www.ethiopianorthodox.org

# የመጨረሻው ተጠሪ ሐዋርያ

ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል ቅዱስ እንድርያስ የመጀመሪያው ተጠሪ ሐዋርያ ሲባል ቅዱስ ማትያስ ደግሞ የመጨረሻው ተጠሪ ሐዋርያ ይባላል ምክንያቱም ማትያስ ከሐዋርያት ጋር ለሐዋርያነት አልተጠራም ጌታችን ካረገ በኋላ በአስቆሮቱ ይሁዳ ቦታ የገባ ሐዋርያ ነው ። አመራረጡም በዕጣ ነው እርግጥ ከዕጣው በፊት ጸሎት ተደርጐ አል ።

የቅዱስ ማትያስ ስም በሐዋርያት ሥራ ፩ ፡ ፲፭ - ፳፮ ላይ ከመጠቀሱ በቀር በሐዲስ ኪዳን ውስጥ በሌላ ቦታ ተጠቅሶ አይገኝም ከዚህም ሌላ ጌታችን ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ለሌሎቹ ሐዋርያት በተገለጠ ጊዜ ለማትያስ እንደተገለጠለት የሚናገር ክፍል የለም ። እንደዚሁም ጌታችን "ሂዱና አስተምሩ" የሚለውን ትእዛዝ ለደቀመዛሙርቱ ሲሰጥ ማትያስ እንደነበረ አልተገለጠም ።

ይሁን እንጂ ማትያስ ለሐዋርያነት እንዲመረጥና ዮስጦስ መርስያስ ከተባለው ከዮሴፍ ጋር ዕጣ እንዲጣጣል ሀሳብ ያቀረበው ቅዱስ ጴጥሮስ እንደተናገረው ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ መድኃኒታችን ኢየሱስ እስከ ዐረገበት ቀን ድረስ በሐዋርያት መካከልም በገባበትና በወጣበት ዘመን ሁሉ ማትያስ ከሐዋርያት ጋር እንደነበረ የሐዋርያት ሥራ ፩ ፡ ፳፩ - ፳፪ ያሳያል ። በዚህም መሠረት ትንሣኤውን አይቷል ። በማየቱም ለትንሣኤው ምስክር እንዲሆን ተመርጦአል ።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊነቱ የታወቀው አውሳብዮስ ቅዱስ ማትያስ ከሰብዓው አርድእት አንዱ እንደነበረ ጽፎአል ። (አው፩ ፡ ፲፫ ፡ ፫) በዚህ መሠረት ማትያስ ከጥንት ጀምሮ ክርስቶስን የተከተለ ፣ ለማስተማርም ከሰብዓው አርድእት ጋር ልዩ ትእዛዝን የተቀበለ ነው ። (የሐዋ. ፲ ፡ ፩) በበዓለ ሐምሳም ዕለት መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎአል ።

የቅዱሳን ሐዋርያትን ሥራ በሚናገረው ገድለ ሐዋርያት በተባለው መጽሐፍ ስለ ቅዱስ ማትያስ የሚከተለው ታሪክ ተጽፎአል ። "ሐዋርያት በዕጣ ወደ የሀገረ ስብከታቸው ሲሄዱ ማትያስ ወደ ሀገረ በላዕተ ሰብእ እንዲሄድ ዕጣ ወጣለት"ይህ ሀገር በየትኛው ክፍለ ዓለም እንደነበረ ዛሬ አይታወቅም "የዚህ ሀገር ሰዎች የተለመደ የአውሬ ጠባያቸውን በአንድ እንግዳ ሰው ላይ ከመፈጸማቸው በፊት ዓይኑን ያሳውሩታልእስከ፴ቀንምድረስእንደእንስሳ ሣር ያበሉታል ። ማትያስም ሰው ይበላሉ ወደሚባሉት ሰዎች ሀገር በደረሰ ጊዜ ዓይኑን በሥራይ አሳወሩትወደ እስር ቤትም አስገቡት ። ሣርም እንዲበላ አስገደዱት እርሱ ግን ለመብላት አልፈቀደም የእግዚአብሔር ኃይል ከእርሱ ጋር ስለነበር ምንም ጉዳት አልደረሰበትም ።

ማትያስ በእስር ቤት ሁኖ ሲጸልይ ፴ ቀን ከመሙላቱ አስቀድሞ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ እንድርያስን ላከለት እንድርያስም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እየተመራ ማትያስ ካለበት እስር ቤት ገባ ማትያስንም ሲዘምር አገኘው በዚህ ጊዜ ሁለቱ ቅዱሳን "እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ ።" የተባለው ቃል እንደ ተፈጸመ ተወያዩ ።

ቅዱስ ማትያስ ከእስር ቤት በወጣ ጊዜ ፻፳፫ሰዎች ከእርሱ ጋር ወጥተዋል። በዚያ ሀገር ሰዎችም ይህን አምላካዊ ኃይል በማትያስ ላይ ከተመለከቱ በኋላ በክርስቶስ አምነዋል ሐዋርያው ማትያ ስም በክርስቶስ ያመኑትን አጥምቆአቸዋል ለሰይጣን ይሰግዱባቸው የነበሩትን ቤቶችን አፍርሰው አብያተ ክርስትያናትን እንዲያንፁ መክሮአቸዋል ። (ገ.ሐ.ገጽ ፪፻፳፭ - ፪፻፵፫ በሎንዶን የታተመ)

ቅዱስ ማትያስ በትምህርቱ ላሳመናቸው መጽሐፍ ጽፎላቸው እንደነበር እንደ እነቀሌምንጦስ ያሉ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በመጽሐፋቸው ጠቅሰዋል ጥቅሱም እንደዚህ ይላል ። "ከአንተ በፊት የነበሩ ነገሮችን ማድነቅ ተጨማሪም ዕውቀት ለማግኘት ይህን የመጀመሪያ ደረጃ አድርግ በማለት ማትያስ እንደመከረን የእውነት መጀመሪያ ማድነቅ ነው" ከዚህም ጋር ከማትያስ ትውፊታዊ ወንጌል የተገኘ እየተባለ የሚጠቀስ ቃል አለ ። ይኸውም የሚከተለው ነው "ማትያስም አስተማረ እንዲህም አለ ፣ ከሥጋ ጋር መታገል ለሥጋዊ ምኞትም ድል አለመሆን ይገባል ፣ ነገር ግን ነፍስን በእምነትና በዕውቀት ማሳደግ ይገባል" (የአዲስ ኪዳን አዋልድ ገጽ ፲፱ - ፶፫)

ቅዱስ ማትያስ በመጨረሻ ወደ ደማስቆ ሄዶ ወንጌልን ሲያስተምር ሳለ የደማስቆ ሰዎች በብረት አልጋ ላይ አጋድመው ከታች እሳት አነደዱበት ። ይህን አይነት ሥቃይ እስከ ፺ ቀን ድረስ ከፈጸሙበት በኋላ በሰባተኛው ቀን ሄደው በሰውነቱ ምንም ዓይነት ጉዳት ሳይደርስበት አገኙት እንደገናም እሳቱን አብዝተው ቢያነዱት ምንም ሊያቃጥለው አልቻለም ። በዚህ ጊዜ ይህን ሥቃይ ይፈጽሙበት የነበሩ ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ አምነው ተጠመቁ ከዚህ በኋላ ሐዋርያው ማትያስ በእስራኤል ሀገርበይሁዳውስጥእያስተማረናምእመናንን እየመራ ቆይቶ ፊላዎን በተባለች ቦታ በሽምግልና ዐርፎአል ።

ሐዋርያው ማትያስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ መታሰቢያው መጋቢት ፰ ቀን ይከበራል በምዕራብ ቤተ ክርስቲያን እንደ አውሮፓ የቀን አቆጣጠር የካቲት ፳፬ ቀን በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤ/ ክርስቲያንም ነሐሴ 9 ቀን (እ.አ.አ.) ይከበራል ።

"የተጠሩ ብዙዎች ናቸው የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸው ።" እንደተባለው ይሁዳ ለሐዋርያነት ተጠራ ግን የመጨረሻውን የሐዋርያትን ዕድል ሳያገኝ ቀረ በእርሱም ፋንታ ባዕድ ማትያስ ተመረጠ የሐዋርያነቱንም ሥልጣን ወሰደ ። ስለ ክርስቶስም እስከ መጨረሻ ሕይወቱ ምስክር ሆነ ።

በዚህአንፃርእንደሐዋርያውማትያስ የሐዋርያትአንድነትበሆነችውበቅድስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚኖሩ ሁሉ በኋላ ተነሥተው ከፍተኛ ሐዋርያዊ ክብርን ያገኙ የክርስቶስ ጸጋ ከረፈደና ከመሸ መጥተው በእምነትና በምግባር የተሰለፉትን ከጡዋት ጀምረው እስከ ማታ ከሠሩት ጋር ታስተካክላለችና ። ይህም በፊያታይ ዘየማን ታይቷል ። በጳውሎስም ተረጋግጧል ።

እነሆ ከመጀመሪያ የተጠሩ ቢኖሩ ጥሪውን ካላከበሩ እንደ ይሁዳ ዋጋ አይ

---

ድጐ ይመግበዋል ፣ ነገር ግን ሰው ከፈጣሪው ትእዛዝ ወጥቶ በበደለ ጊዜ እነ ዚህ ለአገልግሎት የተፈቀዱለት ዐሐይ ነፋስና ዝናብ ሊጐዱት ይችላሉ ። ብለዋል ቅዱስነታቸው እንደተናገሩት ።

ለእኛ ጥቅምና አገልግሎት የተፈጠሩት ፍጥረታት ሁሉ እኛን እንዳይጐዱንና ችግርንና መከራን እንዳያመጡብን የፈጣሪያችን ትእዛዝ ጠብቀን እንራመድ ይህንንም ያደረግን እንደሆን እግዚአብሔር በፍጥረቱ ደስ ይለዋል እንደ ተባለው ፈጣሪያችን በምንሠራው ሥራ ሁሉ ደስ ይለዋል ።

ቄ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ



# የቤተሰብ ዓምድ
## የሚታዘዙ ልጆች የሚያገኙት በረከት

እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፦ "እኔ የማደርገውን ነገር ሁሉ ከአብርሃም አልሠውርም ምክንያቱም አብርሃም በዕውነት ታላቅና ብርቱ ሕዝብ ይሆናልና የምድር አሕዛብም ሁሉ በእርሱ ይባረካሉ ፣ ጽድቅንና ፍርድን በማድረግ ረገድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቹንም ከርሱም በኋላ የሚነሣውን ቤተሰቡን ሁሉ ማዘዝ እንደሚችል አውቃለሁ " (ዘፍጥ.፲፰፡፲፯-፲፱ )

በማንኛውም ሥርዓተ ማኅበር የሚታዘዙ ልጆች ያሏቸው ወላጆች ብፁዓን ናቸው ፤ የማይታዘዙና ጋጠወጥነት የተጠናወታቸው ልጆች ያሏቸው ወላጆች ግን የወላድ መካኖች በመሆናቸው ሊታዘንላቸው ይገባል ፡ ሃምሳ ቢወለድ ሃምሳ ነው ጉዱ ከተባረከ ይበቃል አንዱ የሚሉት ባህላዊ አነጋገርም ያለምክንያት የተወረወረ አይደለም ። ስለዚህም ዋና ቁም ነገር ልጅ ከማግኘቱ ላይ ብቻ ሳይሆን ሠርቶ ቀጥቶ በትምህርት ኮትኩቶ የማሳደጉን ጥበብ ማጥናት ያስፈልጋል ለአብርሃም ከተሰጠውም ብዙ ጸጋ አንዱ ዘርፍ ይኸው ነበር ። ከዚህም የተነሣ "ልጆቹንና ከርሱ ቀጥሎ የሚነሣውን ቤተሰቡን ማዘዝ እንደሚችል አውቃለሁ " ሲል እግዚአብሔር ራሱ መስክሮለታል ።

አዎ ብዙ ወላጆች በልጆቻቸው አለመታዘዝ ምክንያት በበረከት ፈንታ መርገም በደስታም ፈንታ ሐዘንና ፀፀትን አትርፈዋል ። ለአብርሃም የተሰጠው ልጅ ግን እስከሞት ድረስ እንኳ የሚታዘዝ እንደነበር ተጽፎልናል ይኸውም እግዚአብሔር የአብርሃምን እምነት ለመፈተን የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን መሥዋዕት አድርገህ አቅርብልኝ ብሎ ባዘዘው ጊዜ ይስሐቅ ለመሥዋዕትነት የሚቃጠልበትን ዕንጨት ተሸክሞ ከአባቱ ጋር ወደሞሪያ ተራራ ተጉዟል ። ይህም መስቀለ ሞቱን ተሸክሞ ስለሰው ፍቅር እስከቀራንዮ የተጓዘ የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ነበር ። እርሱ (ክርስቶስ) እስከሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ ተብሎ ተጽፎአልና ።

በእግዚአብሔር ቃል ለወላጆቻቸው የሚታዘዙ ልጆች መኖር ራሱ ለአንድ ዓይነት ታላቅ አገልግሎት ለሚመረጡ ሰዎች የመመዘኛ ነጥብ ሆኖ ተገኝቶአል ። ይኸውም "ማዕርገ ቅስና መሾምን የሚወድ ማንም ሰው የማይነቀፍ የአንዲት ሚስት ባል ልከኛና ራሱን የሚገዛ ሥራ ወዳድ እንግዳ ተቀባይ የሆነ ለማስተማር ብቃት ያለውም የማይሰክርና የማይከራከር የገንዘብ ፍቅር የማያሸንፈውና ልጆቹን በጭምትነት ይዞ የራሱን ቤት በመልካም ሁኔታ ማስተዳደር የሚችል መሆን አለበት ይላል ሐዋርያ ጳውሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ጢሞቴዎስ በላከለት ቃል (፩ ጢሞ ፫ ፡ ፩-፭ )

የልጆች አስተዳደግ መበላሸትና የመታዘዝ ጉድለት ጉዳት ወላጆችን በማሳዘን ብቻ የሚወሠን አይደለም ፤ ሀገርንና ወገንን ቤተ ክርስቲያንንም ጭምር የሚያሳዝን ፀፀትን የሚያተርፍ ሊሆን ይችላል ። ታሪክን የሚያሳድፍ ሥነ ምግባርን የሚያጐድፍ ልጅ ከመውለድ ይልቅ መካንነት ይመረጣል ።

---

ኖራቸውም ቀድሞ ያልተጠሩ ቢኖሩ ደግሞ ራሳቸውን ቢያዘጋጁ እንደ ማትያስ በመጨረሻ ይጠራሉ የቃሉም መስካሪዎች ይሆናሉ እንደ እነዚህም ያሉት እጅግ ዕድለኞች ናቸው ። ከመጀመሪያው ይልቅ መጨረሻው ያማረለት ብፁዕ ነውና ።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org

እንግዲያውስ ልጆቹን የመውለድ ፍላጎት በእግዚአብሔር ቃል ተከባክቦ ለማሳደግ ከሚያስችል ጥበብ ጋር የተቀናጀ መሆን ይገባዋል ። መካኖች ልጅ በማጣታቸው የሚያዝኑትን ያህል የልጆቻቸው ጠባይ ተበላሽቶባቸው መላ የጠፋቸው ወላጆችም አሉ ። ስለዚህም መውሰድ ብቻውን ከመካንነት የተሻለ መሆን አያስችልም ።

ከዐሥሩ ትእዛዛተ እግዚአብሔር አንዱ ዋና ክፍል "እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ ይረዝም ዘንድ አባትህንና እናትህን አክብር" የሚል ነው ። ሰሎሞንም በምሳሌው "ልጄ ሆይ የአባትህን ምክር ስማ ፤ የእናትህንም ሕግ አትናቅ(ምዕ ፩፡፰) እናንት ልጆች የአባትን ተግሣጽ ስሙ ማስተዋልንም ታውቁ ዘንድ አድምጡ (ምሳ. ፬፡፩) ይላል ።

ከዚህም ጋር የሚተባበር የሐዲስ ኪዳን ቃል "ልጆች ሆይ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ ይህ የሚገባ ነውና መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር ፤ እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት እናንተም አባቶች ሆይ ልጆቻችሁን በጌታ ምክር በተግሣጽ አሳድጓቸው እንጂ አታስቆጧቸው ' የሚል ነዋ (ኤፌ.፩፡ ፩-፬)

ከዚህም ውጭ ልጆችን ስድ በመልቀቅ አሞላቀው በማሳደግ የሞራል ስብራት ገጥሞአቸው ራሳቸውን ለመቆጣጠር እንዲሳናቸው የሚያደርጉ ወላጆች ቢኖሩ ድርጊቱ ከነፍስ ገዳይነት ተነጥሎ የሚታይ አለመሆኑን የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል ።

መ/አዕ መክብብ አጥናው

# ዜና ሊቃውንት

መምህር ገብረ እግዚአብሔር ኃይሉ በትግራይ ክፍለ ሀገር በዓድዋ አውራጃ ልዩ ስሙ የሐ ደብረ ሐመልማል (መዝብር) በተባለው ቀበሌ ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፳፮ ዓ.ም. ከአባታቸው ከአለቃ ኃይሉ ወልደ ማርያም ከእናታቸው እመት ዘነበች ወልደ ማርያም ተወለዱ ።

እድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ ከአጎታቸው ከቄስ ገብረ ሕይወት ወ/ማርያም ትምህርት ጀምረው ትምህርቱ እየገባቸው ሲሄድ ወላጆቻቸው መሪጌታ ተክለ ጊዮርጊስ ከሚባሉ መምህር አስገብተዋቸው ንባብና የቃል ትምህርት በማጠናቀቅ የግብረ ዲቁናን ትምህርት ተማሩ ።

ሆኖም የትምህርት ፍላጐታቸው እየተጠናከረ በመሄዱ ከወላጆቻቸው ጋር ሆነው የፈለጉትን ትምህርት ለመከታተል ያለመቻላቸውን በመረዳት ከትውልድ አገራቸው ወጥተው ደብረ ዓባይ ወደሚባለው የመዝገበ ቅዳሴ ማስመስከሪያ የአብነት ቦታ ገዳም በመሄድ ምስክር ከሆኑት ሊቅ ከመምህር የኋላሸት መንገሻ ምዕራፍ ጾመ ድጓ ፤ ባሕረ ሐሣብና የመዝገበ ቅዳሴ ዜማ ልኩን ፤ አመሉንና ተቃራኒውን ለይተው ለመምህርነት በሚያበቃ ደረጃ ስለወሰኑት በመምህርነት ተመርቀዋል ።

ከዚያም በኋላ በዚሁ ገዳም ቅዳሴ እያስተማሩ ከመሪ ጌታ መጽሐፍ ቅኔ ተምረዋል በዚህም ሳይወሰኑ የቅኔ ሞያቸውን ለማዳበር ከደብረ ዓባይ ተነስተው ወደ ጎንደር ክፍለ ሀገር በመሄድ በሊቅነታቸው ከታወቁት ከመምህር አክሊሉ ገ/ሥላሴ ዘንድ ቅኔቤት ገብተው ለአምስት ዓመት ያህል ቅኔ ከነአገባቡ ከመማራቸውም በላይ የዳዊትንና የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜንም ከርሳቸው አካሂደዋል ።

ከዚያም ወደነበሩበት ገዳም ወደ ደብረ ዓባይ ተመልሰው በዚያው ቅዳሴ እያስተማሩ ለ፯ ዓመታት ያህል ከኔታ የኋላሸት ጉባዔ ፤ መጻሕፍተ ሐዲሳትን አሂደዋል በዚህም ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ወደትውልድ አገራቸው ተመልሰው ከአቡነ መዝራዕተ ክርስቶስ ገዳም ወምበር ዘርግተው ጉባዔ አስፍተው ለ፲፪ ዓመታት ያህል በአፍለኛው ጉባዔያቸው ጠንክረው በማስተማር ብዙ ዲያቆናትን ቀሳውስትና መምህራንን አፍርተዋል ። ስለሆነም በማስተማር ላይ እንዳሉ የፊተኛው መምህራቸው የኔታ የኋላሸት አንድ የታመኑ አባት መነኩሴ ልከው እፈልግሃለሁና ቶሎ እንድትመጣ ሲሉ ስለላኩባቸው መልእክቱን በመቀበል የአቡነ መዝራዕተ ክርስቶስ ገዳም መምህርንና ማህበሩን አስፈቅደው ወደ ደብረ ዓባይ ሄዱ ።

እንደሄዱም የኔታ የኋላሸት በናፍቆት ሲጠብቋቸው በመምጣታቸው ተደስተው ወዲያው ከባና ጥንግ ድርብ ሙሉ የመዓርግ ልብስ ሸልመውና መርቀው እንግዲህ ወዲህ ቤቴንና ጉባኤን የምትወርሰው አንተ ነህና ከአቡነ መዝ



መ/ገብረ እግዚአብሔር ኃይሉ

ራዕተ ክርስቶስ ያሉ ተማሪዎችህ የሚሰናበቱትን አሰናብተህ ካንተ ጋር ሊመጡ የሚገባቸውን ይዘሃቸው እንድትመጣ በማለት አባታዊ ምክር መክረው ሰደዷቸው ።

ከዚህም ጋር ያስተምሩበት ለነበረው



ገዳም መምህር ወማህበር እንዲህ የሚል መልእክት ልከው ነበር "ፍቁራን አባቶቼና ወንድሞቼ ሰላመ እግዚአብሔር ይድረሳችሁ የመንፈስ ቅዱስ ልጄ አባ ገብረ እግዚአብሔር ከወጣትነቱ ጊዜ ጀምሬ ይሆነኛል እመገበዋለሁ በማለት አርሜ ኮትኩቼ በማሳደግ ለፍሬ ያደረስኩት ፍሬው የናንት ምግብ ሆኖ በመገኘቱ ፈጣሪዬን አመስግኜ አልጠግበውም ።

ነገር ግን በኔ ወምበር የሚተካ እርሱ ነውና በእርሱ ወምበር ተተክቶ የሚያስተምር ሰው ሰጥታችሁት እርሱን ግን አቡነ ዘሰማያት ሰጥታችሁ እንድትልኩልኝ አደራ በማለት ልከው ነበር ።ዳሩ ግን ከጉባዔው ስፋት ከተማሪዎቹ ብዛት የተነሣ ማህበሩ ሊሰዷቸው ስለአልፈቀዱ በየምክንያቱ ለ፪ ዓመት ያህል ቆዩ ።

በዚህም ሁኔታ የደብረ ዓባይ ገዳም መምህርና ማህበር ሕዳር ፲፬ ቀን ፳፪ ዓ. ም. በገዳሙ ማህተም አትመው እንደሚከተለው ጽፈው ደብዳቤ ላኩላቸው ለውድ ልጃችንና አለኝታችን አባ ገብረ እግዚአብሔር ኃይሉ ወልዱ ለሳሙኤል ወላዴ እእላፍ ውድ ልጃችን ! የምናሳስብህ እንደ ምታውቀው አባትህ የኔታ የኋላሸት በአሁኑ ጊዜ ሕመሙ እየጸናባቸው ስለሄደ ጉባዔው እንዳይፈታብን መጥተህ በሳቸው ወምበር ተተክተህ እንድታስተምርልን ይሁን ።

ጥንትም ቢሆን ብዙ ይወልዱ ሞያውንና ግብሩን አይተው አንዱን ይወዱ እንደሚባለው በትምህርትና በትሩፋት ኮትኩተው ያሳደጉህ ለዚህ ነውና ለኛም በሳቸው ወምበር የምትተካ አንተ እንደሆንክ ከአስር ዓመት በፊት ራሳቸው ነግረውናል ።

ስለዚህ ቶሎ እንድትመጣ ይሁን ሰላምና ጤና ክብርና ሞገስ ላንተ ይሁን መምህር ወማህበር ዘደብረ ዓባይ ቅድስት የሚል ነው ።

በዚህ መሠረት ደብረ ዓባይ ሂደው በሕመም ላይ ከነበሩት መምህራቸው ተገናኝተው ወምበሩን ተረክበው መምህራቸውን እያስታመሙና እያስተማሩ አንድ ወር እንደቆዩ የኔታ የኋላሸት የጻድቁ የአቡነ ሳሙኤል ዓመታዊ የዕረፍታቸው መታሰቢያ ታህሣሥ ፲፪ ቀን እንደተከበረ በማግሥቱ ታህሣሥ ፲፫ ቀን ፳፪ ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ።

ከዚህ በኋላ መምህር ገብረ እግዚአብሔር በተሰጣቸው አደራ መሠረት በቦታው ተተክተው ሲያስተምሩ ከቆዩ በኋላ በጊዜው የትግራይ ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በመቀሌ ከተማ ያሠሩት ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት የካህናት ማሠልጠኛ አዳሪ ቤት ስለሆነ ብዙ ውጤትና ብዙ ፍሬ ለቤተ ክርስቲያናችን የሚያፈሩ መሆናቸውን ደጋግመው ስለጸፉላቸውና አስጠርተውም ስለ ነገሩዋቸው ቀደም ሲል ከቦታው አብረዋቸው ከኔታ የኋላሸት የተማሩ አባት ቄስ ገበዝ ገብረ ሊባኖስን ተክተው በ፳፫ ዓ.ም. ወደ መቀሌ መጡ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ጉባዔ አስፍተው በከሣቴ ብርሃን ሰላማ መ/ተ/ቤት በማስተማር ላይ ይገኛሉ ሆኖም ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በ፸፩ ዓ.ም. አገልግሎታቸውንና ትጋታቸውን ተመልክተው መልአከ ሰላምየሚለውንየመዓርግስም ሰጥተው በመምህርነታቸው ላይ በተደራቢነት የደብረ ሰላም ቅ/ሚካኤልን ደብር እልቅና ሰጥተዋቸው በማስተዳደር ላይ ናቸው ።

መልአከ ሰላም ገብረ እግዚአብሔር በየጊዜው በትጋት አስተምረውና አሠልጥነው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ካበቋቸው እጅግ ብዙ ከሆኑት ዲያቆናትና ቀሳውስት መካከል በመምህርነት ሞያ ተመርቀው በየቦታው ወምበር ዘርግተው ዛሬ በማስተማር ላይ የሚገኙት መምህራን ደቀመዛሙርቶቻቸው ዋና ዋናዎቹ ስማቸው እንደሚከተለው አቀርበነዋል ።

፩ኛ/ አባ አረጋዊ ገ/እግዚአብሔር
፪ኛ/ አባ ኃይለ ጊዮርጊስ ገ/አፍጼ
፫ኛ/ መሪጌታ ሐዲስ ማቴዎስ
፬ኛ/ መሪጌታ ጽጌ ሃይማኖት
፭ኛ/ መምህርት ኢየሩሳሌም ተፈሪ
፮ኛ/ አባ ወልደ ኪዳን ገ/እግዚአብሔር
፯ኛ/ አባ ገ/ማርያም ክንፈ ገብርኤል
፰ኛ/ አባ አምሃ ሥላሴ ገ/ሕይወት
፱ኛ/ አባ ተስፋ ማርያም
፲ኛ/ መልአከ ስብሐት ተክለ ሃይማኖት አበበ አክሱም
፲፩ኛ መልአከ ምሕረት ዓምደ ብርሃን ገ/ጻድቅ አ.አ
፲፪ኛ/ አባ ዘርዓ ቡሩክ ኃይሉ
፲፫ኛ/ አባ ገብረ ዮሐንስ
፲፬ኛ/ አባ ኃይለ ሚካኤል በየነ
፲፭ኛ መሪጌታ ሐዲስ ዓምዱ
፲፮ኛ መሪጌታ ሐረገ ወይን ወ/ጊዮርጊስ
፲፯ኛ መሪጌታ ይስሀቅ ተክለ ሃይማኖት ዓድዋ
፲፰ኛ መሪጌታ ተክለ ሥላሴ ወ/ጊዮርጊስ
፲፱ኛ " ዕዝራ ተስፋ ኢየሱስ እንደርታ
፳ኛ/ መሪጌታ እንድርያስ ለገሠ ወሊጋ
፳፩ኛ/ መሪጌታ ረዳኢ
፳፪ኛ/ መምህር ገ/ዮሐንስ ተመስገን ተንቤን
፳፫ኛ/ አባ ዘርዓ ቡሩክ ገ/ሚካኤል
፳፬ኛ/ መሪጌታ ይስሀቅ አድኃና
፳፭ኛ/ አባ ገብረ ሥላሴ ወ/ሥላሴ ናቸው እነዚህ ከላይ ስማቸው የተዘረዘረው በቡቂ የመዝገበ ቅዳሴ ሞያ ተምረው በመምህርነት የተመረቁት ብቻ ናቸው እንጂ ለዲቁና ለቅስና አገልግሎት ያበቋቸው ደቀ መዛሙርት እጅግ ብዙ ናቸው ።

መልአከ ሰላም ገብረ እግዚአብሔር በታወቀው የመዝገበ ቅዳሴ ሞያቸው በተሰጣቸው የመዓዛ ክህነት ሀብት ልዩ ተሰጥዎ ያላቸው ድምጻዊ ከመሆናቸው የተነሣ ከጥንት ከአበው ሲያያዝ የመጣውን የደብረ ዓባይ ባሕል የቅዳሴ ዜ



www.ethiopianorthodox.org

ማ አብነት ግዕዙና ዕዝሉ እንዲሁም አ ራራዩና እንቀጹ ሳይቀር በሙሉ በዘ መናዊ መማሪያ የድምጽ መቅረጫ ቴፕ ተቀርጾ በቅርስነት ለትውልድ እንዲተ ላለፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስብከተ ወንጌልና ሐዋ ርያዊ ተልዕኮ መምሪያ በተወሰነው መ ሠረት ድምጻቸው ተቀርጾ የቅዳሴው ካ ሴት ለሚፈልግ ሁሉ እየተሸጠ በአገልግ ሎት ላይ ይገኛል በዚህም ከፍተኛ አገ ልግሎት ለቤተ ክርስቲያን ማበርከታ ቸውን በመረዳት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያር ክ አባታዊ መታሰቢያ ስጦታ የአንገት ሐይክል ዕፀ መስቀል ሸልመዋቸዋል ።

መልአከ ሰላም ገብረ እግዚአብሔር በአሁኑ እድሜያቸው ፶፩ ዓመት የሆና ቸው ሲሆን በ፲፱፻፵ ዓ.ም. መዓርገ ዲ ቁናን ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ ጳጳስ ዘኤ ርትራ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. መዓርገ ምንኩስ ናን ከመምህር ዘሚካኤል ዘደብረ ዓባይ ገዳም መምህር (አበምኔት) ፣ በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም መዓርገ ቅስናን ከብፁዕ አቡነ ሚ ካኤል ዘጎንደር ፣ በ፲፱፻፸፱ ዓ.ም መዓር ገ ቁምስናን ከብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ዘት ግራይ ተቀብለው በዚህ ሁሉ መንፈሳዊ መዓርጋቸው በንጽሕና በድንግልና የ ሚኖሩ አባት ናቸው ።

ከዚህ በቀር መልአከ ሰላም ገብረ እግ ዚአብሔር ኃይሉ ትሕትናን አፍቅሮ ቢ ጽን አክብሮ ሰብእን ዓላማ አድርገው የሚኖሩ በተማሪዎቻቸው ዘንድ ተወዳ ጅነት ያላቸው በአባትነታቸው በምዕ መናንም በኩል ብዙ ፍቅርን ያተረፉ በ አጠቃላይ በአርአያነታቸውና በግብረ ገብነታቸው ተስፋ የሚጣልባቸው ደግ አባት በመሆናቸው ዛሬም በዓላማቸው ጸንተው ከ፻ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎችን በማስተማርና ቤተ ክርስቲያንንም በቅ ን መንፈስ በማስተዳደር ላይ ይገኛሉ ።

ከደቀ መዛሙርቶቻቸው አንዱ

መ/ም/ዓምደ ብርሃን

# የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም
## (ዮሐ. ፲፬-፳፬)

ብዙ ሰዎች የፈጣሪያቸውን የእግዚ አብሔርን ትእዛዝ አይጠብቁም ። እን ዲሁም የበላዮቻቸውን ቃል እያከበሩም አንዳንድ ልጆችም የወላጆቻቸውን መ ልእክት ተቀብለው አይፈጽሙም ። በ ዚህ ምክንያትም በእያንዳንዱ ቤትና በ አንዳንድ መ/ቤት፣የመረረና የከረረ ጸብ ና ንትርክ ሲፈጠር ይታያል ። መድኃኒ ታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአስተማረበ ት ዘመንም በሰዎቹ መካከል ይህን የመ ሰለ የማይገባ ሥርዓት እንደነበረ በአን ድ አባትና በሁለት ልጆች የሰጠው ም ሳሌአዊ ትምህርት ማስረጃ ይሆናል ።

ምሳሌው "ሁለት ልጆች ያሉት አን ድ ሰው ነበረ ብሎ ይጀምራል ። አባት ዬው አንደኛውን ልጁን ጠርቶ ዛሬ ወደ ወይኔ ሥፍራ ሂድና ሥራ ቢለው አልሄ ድም አለው ወደ ሁለተኛው ተመለሰና ወደ ወይኑ ቦታ እንዲሄድ ቢያዘው ለ ጊዜው እሺ አባቴ እሄዳለሁ ብሎ ሳይሄ ድ ቀረ ነገር ግን የመጀመሪያው ልጅ አልሄድም ብሎ አባቱን እንዳስቀየመ ተረድቶ ተጸጽቶ ወደ ወይኑ ቦታም ሄደ ና ተልእኮውን ፈጸመ ከሁለቱ የአባቱን ትእዛዝ የፈጸመ የትኛው ነው ? ብሎ ለ ካህናት አለቆችና ለሕዝብ ሽማግሌዎች እንደጠየቃቸው በማቴዎስ ወንጌል፳፩ ፳፰-፴፩ ያለው ምንባብ ይነግረናል ።

ተጠያቂዎቹ የፊተኛው ነው ብለው መ ልሰውለታል፡ነገር ግን በየጊዜው ነቢያ ትን እያስነሣ ቢነግራቸውና ቢያስተም ራቸው እሺ እያሉ ትእዛዙን ችላ እንደ ሚሉ ሁለተኛም እንሰማም ትእዛዙንም አንፈጽምም እያሉ በሥጋዊ መንገድ ሲሄዱ ኖረው በመጨረሻ ወረደ ተወለ ደ ተሰቀለ ፣ ሞተ ተቀበረ ብለው ወንጌ ላውያን ሲያስተምሯቸው በአድራጎታ ቸውና በስሕተታቸው ሁሉ ተጸጽተው ንስሐ ገብተው የራሱ ወገኖች እንዳደረ ጋቸው መናገሩ ስላልገባቸው በምሳሌ የሰጣቸውን ትምህርት አልተገነዘቡት ም ።

እነሆ እኛ አሁን ከምሳሌው የተረዳ ነው አባት የተባለው እግዚአብሔር አብ ልጆች የተባሉ ደግሞ አዳምና ዘሮ ቹ ሲሆኑ እነዚህም በሁለት ክፍሎ በም ሳሌ መናገሩን ያመለክታል ፣ እኩሌቶ ቹ እግዚአብሔርን ያገለግላሉ የእግዚአ ብሔር ልጆችም ይባላሉ ፣ ገሚሶቹ ደግ ሞ ቃሉን እየሰሙ እንዳልሰሙ እያዩ እ ንዳላዩ በአፋቸው አማኞች ይመስላሉ አምላክ እንዳለም ይናገራሉ በትእዛዙ መሄድ ትእዛዙን መፈጸም ግን አይችሉ ም ይደክማሉ ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "የ ማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም" ያለው ም በአባትነቱ መጠን ያዘዘንን ሳንፈጽ ም ስንቀር ከአባትነቱ እንደሚለየን ከ ጥቅሱ መረዳት ይቻላል ። የእግዚአብ ሔር ልጅነታችን አምነን ቃሉን ብንጠ ብቅ ትእዛዙን ብንፈጽም ይወደናል ፣ ልጆቼም ብሎ ይጠራናል ፣ ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን የማይወደኝ ቃሌን አይጠ ብቅም " ያለውም ስለዚህ ነው ።( ዮሐ ፲፬ ፡ ፳፫ ።)

ቃሉም ትእዛዙም ከባዶች አይደሉም ይኸውም አንደኛ እግዚአብሔር አምላ ክህን በፍጹም ነፍስህ በፍጹም ኃይልህ ና በፍጹም ሀሳብህም ውደድ የሚል ሲ ሆን ሁለተኛው ደግሞ ባልንጀራህን እ ንደራስህና እንደነፍስህ ውደድ የሚሉ ናቸው ። እግዚአብሔር አምላክህን በፍ ጹም ነፍስህና በፍጹም ኃይልህ ውደድ ማለትም ሁሉን የፈጠረ ሊገድል ሊያድን ሊያፀድቅ ሊኮንን ሊሰጥ ሊነሣ የሚችል አንድ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ማወ ቅ፡በልዩ ልዩ ከንቱ አምልኮ መማጸን ከ ኃጢዓት ሁሉ የከፋና ወ ደዘለዓለም ሞት የሚወስድ መሆኑን አውቆ በአንድ እግ ዚአብሔር ብቻ መታመን እንደሚገባ ነው ።

ባልንጀራህን ውደድ ማለት ደግሞ ዘመድህ የሥጋ ወንድምህ ወይም የም ታውቀውና በአምቻና በጋብቻ የተዋወ ቅኸውን ብቻ ሳይሆን በመልክህና በም ሳሌህ የተፈጠረ ሁሉ ወንድምህ መሆ ኑን አውቀህ እንደሚርበኝ ይርበዋል እ ንደሚበርደኝ ይበርደዋል እንደሚጠ ማኝ ይጠማዋል ብለህ ካለህም ከፍለህ ስጠው አብላው አልብሰው አጠጣው አገርሰው ማለት ነው ።

እነዚህን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የማይከተልናየማይፈጽም ሰውካለ ግን "የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል አባቴም ይወደዋል" ተብሎ የተነገረው ቃል ተለይቶታል እግዚአብሔር አም ላኩንና መሰል ወንድሙን የማያውቅና የማይወድ ሁሉ ዓይነ ልቦናው ታውሮ አልና ሥጋዊ ለሥጋው ብቻ የሚኖር በ ዚህ ዓለም ምኞት የታወረ ከንቱ ፍጥረ ት ነው ማለት ይቻላል ፣ እንዲህ ዓይነ ቱ ፍጥረት ነቀዝ እንደበላው እህል ትል እንዳበላሸው ዛፍ አወዳደቁ የከፋ ይሆ ናል ።

በአንድ አገር አንድ ቁመቱ በጣም ረጅም ቅርንጫፉ እጅግ የተንሰራፋ ቅ ጠሎቹም በመልካም ውበት ያሸበረቁ ዛፍ ነበር ይህ ዛፍ ትልቅ የእንጨት ትል በሥሩ ገብቶ ውስጥ ውስጡን እስከ አና ቱ ድረስ እየቦረቦረ በላው ። አንድ ቀን ኃይለኛ ነፋስ ቢነፍስ ከወገቡ ቅርድድ ብሎ ወደቀ በአካባቢው የነበሩት ሰዎ ች የዛፉን ተቀርድዶ መውደቅ አይተው ምክንያቱን ለማወቅ ቀረብ ብለው ተ መለከቱት እነሆ ውስጡ ሙልጭ ብሎ ተበልቶ ባዶ ሁኖ አገኙት ። ይህ ዛፍ አ ቋሙ ቅርንጫፉና ልምላሜው በጣም ያማረ ነበር ። እንኳን እንዲህ ወድቆ ለ ማየት ይቅርና የትል በሽታም የነካው አይመስልም ነበር ። በማለት እጅግ ተ ገርመው ሄዱ ይባላል ።

ከዚህ ታሪክ ብዙ ትምህርት እናገኛ ለን ።በመሠረቱ ዛፉን በሰው ትሉን በዲ ያብሎስ እንመስለዋለን አንዳንድ ሰዎች በዕውቀታቸው በሃብታቸውና በንብ ረታቸው በጣም የታወቁ ሁነው ሳለ ው ሳጣዊ ሰውነታቸው ደግሞ በልዩ ልዩ ኃጢአት ተበላሽቶ ሳይታመሙ ዕገሌ ሞተ ሲባሉ ይሰማሉ ። ዛፉን የሚመለከ ተው ሁሉ በልዩ ልዩ አመለካከት ያየ ው ነበር ። እኛ ከብቶቻችንን እንጠል ልበታለን ብለው ተስፋ የሚጥሉበት ነ በሩ አንዳንዶቹ ደግሞ ይህስ ዛፍ ሰፊ አ ዳራሽ ሠርቶ ገበን ቢያደርጉት እንዴት መልካም በሆነ ነበር እያሉ የሚመኙም ሳይኖሩ አልቀረም ። በማገዶ የተቸገሩ ትም ይህንዛፍ ከሥሩመንግሎበመቁረ ጥ ሳይሆን ቅርንጫፉን ጨፍጭፎ ለብ ዙ ጊዜ ማገዶ ባገለገለን ነበር ሳይሉ እን ዳልቀሩም መገንዘብ ይቻላል ።

ነገር ግን ዛፉ ሳይታሰብ በድንገት ከ ወገቡ ተቀርድዶ ወደቀና እያንዳንዱ ሰው መጥረቢያ እየያዘ መጥቶ ባንድ ቀን ቆርጦና ፈልጦ ለማገዶ ተሻምቶት ሄደ ። የከንቱ ባለጸጋ ዕውቀትና ሀብት ም እለ ሲሉት በሰይጣን ጦር ተወግቶ ይወድቅና የአንድ ቀን ጉድ ሆኖ ይቀ ራል ። እንግዲህ ከሚያሳዝን አወዳደቅ ለመዳን ራሳችንን መጠበቅ አለብን ይህ የማደርገው ክፉ ሥራ ይህም በልቤ ው ስጥ የማስበው ክፉ ሀሳብ ከሰው እስተ ያየትና ከሰው ዓይን የተሠወረ ነው እያ ልን ራሳችንን አናታልል "በሰዎች መ ካከል ስትሆን ምላስህን ጠብቅ ፣ ለብቻ ህም ስትሆን ልብህን ጠብቅ " ተብሎ እንደሚነገር ሁሉ በእግዚአብሔር አለ ማመን ፣ ርኩሰትና ክፉ ምኞት ቂምና በቀል እነዚህን የመሳሰሉትን ትሎች በ ውስጣችን ከማስተናገድ ይልቅ በፍቅ ር በትሕትና በርኅራኄና በበጎ ምግባር ማሸብረቅ የዘለዓለም ክብር እንደሚያ ስጥ ማመን ይገባል ።

ነገር ግን በራሳችን ኃይልና ማስተዋ ል ይህን ምክር ለመፈጸም ስለማንችል እንዴት አድርገን ልባችንን የፍቅርና የ ትሕትና የርኅራኄና የበጎ ስነ ምግባር እ ናደርገው ሳንል አንቀርም ይሆናል መ ቼም በመልካም እንግዳ የተሞላ ቤት ክፉ እንግዳ ተቀብሎ ለማስተናገድ አያ ስፈልግም በክፉ እንግዳ የተሞላ ቤትም መልካም እንግዳ ተቀብሎ ለማሳረፍ የ ሚችል አይደለም ።

ስለዚህ አስቀድመን ክርስቶስ በልባ ችን ቢኖርና በእርሱም ፍቅር ልባችን ከሞላ ለክፉ ሀሳብና ለክፉ ሥራ ሥፍራ ሊኖረው አይችልም ክፋት ምቀኝነት ተንኮልና ክህደት በልባችን ሥፍራ ለ ማግኘት ቢመላለሱብን እንኳ ሂዱ ቤቱ በመልካም አምልኮ በመልካም ፍቅርና ስነ ምግባር ስለተሞላ ሌላ የምናስተና ግድበት ክፍል የለንም ። ብለን እናባር ራቸው ።

በየዕለቱም በምናደርገውና በሚደር ስብን ነገር ሁሉ ክርስቶስን እናስብ ከእ ርሱ ጋር እንጂ ከፈቃደ ሥጋችን ብቻ እንነጋገር እንመካከርም "ሳታቋርጡ ጸልዩ" የሚለው የሐዋርያው ቃል ሁል ጊዜ በነገር ሁሉ ወደ ክርስቶስ እንድን መለከትና ከእርሱ ጋርም አካሄዳችን እ ናድርግ ዘንድ ያሳስበናል ። ይህን ሁሉ ብናደርግ እርሱ ከክፉ ሁሉ ይጠብቀና ል ። ይወደናል ማደሪያውም ያደርገና ል ። በክርስቶስ ደም የነፃ ልብ የአብና የወልድ የመንፈስ ቅዱስም መኖሪያ መሆኑን እናስተውል እርሱም "የሚወ ደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በ እርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን " ያለውም ስለዚህ ነው ።

ሊ/ትጉሃን ገ/ክርስቶስ ኃ/ማርያም





www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

በመቱ ካህናት ማሠልጠኛ ት/ቤት
ነ9ኛ ጊዜ ከወለጋ ፣ ከከፋና ከኢሉባቦ
ር ተመርጠው የተላኩ ፴፭ ካህናት ኮር
ነቸውን ፈጽመው ጥር ፱ ቀን ፲፱፻፸፯
ዓ.ም. ከብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ የኢሉባቦ
ር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲ
ኖዶስ ዋና ፀሐፊ እጅ የምስክር ወረቀ
ታቸውን ተቀብለዋል ።

የመንግሥታውያንና ሕዝባውያን ድ
ርጅት ተወካዮች የሀገረ ስብከቱ ኃላፊ
ዎች ሠራተኞች የደብር አስተዳዳሪዎች
የሰበካ ጉባዔ አባላት በተገኙበት በተ
ደረገው በዚህ የምረቃ በዓል ላይ ብፁ
ዕነታቸው በማሠልጠኛው ት/ቤት እን
ደደረሱ ተመራቂዎች ካህናትና የሰንበ
ት ት/ቤት መዘምራን የማሠልጠኛው
ልዩ ልዩ ዘርፍ ሠራተኞች አቀባበል
ድርገውላቸዋል ።

ብፁዕነታቸው የምስክር ወረቀቱን
ሲሰጡበት ጊዜ "ሂዱና አስተምሩ" ከ
ለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተነስ
ተው በሰጡት መመሪያ የተሰጣችሁ የ
ምሥክር ወረቀት የሚጠበቅባችሁን ክ
ህነታዊ ግዴታና የኃላፊነታችሁን ክብ
ደት የሚያስገነዝባችሁ ሲሆን የቀሰማ
ችሁትን ትምህርት በትጋትና በንቃት
ካልሳችሁ ለላካችሁ ወገን ካላስተማራ
ችሁ የምስክር ወረቀቱ በእናንተ ላይ
የሚመሰክርባችሁ ነው ብለዋል ፣ ቀጥ
ሎም የዚህ የካህናት ማሠልጠኛ ት/
ቤት ዓላማ እንዲሳካ የተባበሩትን መን
ግሥታውያንና ሕዝባውያን ድርጅቶች
ሠራተኞችን አመስግነው ለወደፊትም
ይህ ዓይነቱ ድጋፍና ትብብር እንደማይ
ለየን እናምናለን ብለዋል ።

ከብፁዕነታቸው ንግግር ቀደም ብለ
ው የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ሊቀ
ኅሩያን ብርሃኑ መንገሻ የካህናት ማሰል
ጠኛው ርዕሰ መምህር አባ ኃይለማርያ
ም ገሠሠ ስለ ማሠልጠኛው ሥራ አፈ
ጻጸም ሪፖርትና ዝርዝር መግለጫ በቅ
ደም ተከተል አቅርበናል ። በዚሁ የም
ረቃ በዓል ላይ በትምህርት ውጤት ብ
ልጫ ላገኙና በጠባያቸው ለተመሰገኑ
ካህናት በብፁዕነታቸው እጅ ሽልማት
የተሰጣቸው ሲሆን በካህናቱ የተሠሩት
የእደ ጥበብ ሥራ ውጤቶች በማሠልጠ
ኛ የሚካሄዱት የልማት ሥራዎችተጐብ



ብፁዕነታቸው የምስክር ወረቀት ሲሰጡ

ኝተዋል ።

በዚህ በ9ኛው ዙር የሰለጠኑት ካህና
ት ከወለጋ ፲፫ ከከፋ ፲፫ ከኢሉባቦር ፱
ናቸው ። በጠቅላላው ማሠልጠኛው ከ
ተቋቋመ ጀምሮ የሰለጠኑት ካህናት ብ
ዛት ፫፻፳ መድረሳቸው ታውቋል ይህማ
ሰልጠኛ እስካሁን በቡኖ አውራጃ በዳ
በና ቀበሌ ላይ የማሰልጠን ተግባሩን ሲ
ያከናውን ቆይቷል ፣ በርካታ ካህናትን
ም አሰልጥኖ አስመርቋል የሰለጠኑትም
ካህናት በስብከተ ወንጌል በመንፈሳዊ
የቤተክርስቲያን አገልግሎት ዘርፍ ከሰ
ጡት ጠቃሚ አገልግሎት ሌላ በበለጡ
ት የሙያ ትምህርታቸው በገበሬ ማኅበ
ራት በአምራቾች ውስጥ አባላት እንደ
መሆናቸው ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ አገ
ልግሎት በመስጠት የሥራን ክቡርነት
በተግባር ጭምር እያሳዩ በአርአያነታ
ቸው የተመሰገኑ ሆነዋል ።

በኢሉባቦር ሀገረ ስብከት በልማት
በኩልም በየአብያተ ክርስቲያናቱ በሰለ
ጠኑት ካህናት የአነስተኛ እደ ጥበብ ሙ
ከራ እየተደረገ ነው ። ለማስረጃም ያ
ህል በቴፒ ከተማ በቅ/ጊዮርጊስ ቤተ ክ
ርስቲያን በሰበካ ጉባዔ ድጋፍ ሰጭነት
በሰልጣኞች ካህናት የተጀመረው የቃ
ጫ ሥራ ፣ በጐሬ አውራጃ በሲቦ ልደ
ታ ቤተ ክርስቲያን የተጀመረው የሽመ
ና ሥራ የካህናት ማሰልጠኛው ሥራ ው
ጤት ናቸው ።

ማሰልጠኛው በቡኖ አውራጃ በዳበ
ና ቀበሌ በነበረበት ወቅት በሁሉም ዘ
ርፍ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል በርካታ
የሰው ጉልበት የገንዘብ ወጭ የጊዜ መ
ስዋዕት ተከፍሎበታል የተገኘው ውጤ
ትም ቀላል አልነበረም ሆኖም ለዘለቄ



ታ ማሰልጠኛው በአስተዳደሩም ሆነ
በልማቱ በሰው ጤንነት ላይ ጭምር ካስ
ከተለው ችግር የተነሳ ሁኔታውን በወ
ቅቱ ለመቆጣጠርና ለማሻሻል በየአን
ጻሩ ጥናትና ሙከራ ሳይደረግ አልቀረ
ም ፣ ዛሬ ጊዜው ሲደርስ የልዑል እግዚአ
ብሔር ፈቃዱ ሆኖ ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ
ሀገረ ስብከቱን በሊቀ ጵጵስና እንዲመ
ሩ ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ አደራና
ኃላፊነት ተቀብለው እንደመጡ ከፊታ
ቸው ከተደቀነው የአሠራርና የአፈጻ
ጸም ችግር አንዱ የዚህ የካህናት ማሠል
ጠኛው ት/ቤት ነበር ።

፩ኛ/ አስተዳደሩ ከመንበረ ሊቀ ጵጵ
ስናው ፩፻፲ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በመ
ሆኑ በመደበኛ የሀገረ ስብከቱ ሥራም
ሆነ በማሰልጠኛው ት/ቤት በቅርብ ቁ
ጥጥርና ክትትል ለማድረግ ያለው የቦ
ታው መራራቅ ፣ አስቸጋሪ ነበር ፣

፪ኛ/ በልማት በኩል ቦታው አትክል
ት ለመትከልና ለማስፋፋት የአየር ጠ
ባዩ ተስማሚ አልነበረም ፣

፫ኛ/ ቦታው በሠልጣኞች ካህናት ጤ
ንነት ላይ የሚያደርሰው ችግር ከፍ ያለ
ነበር ።

፬ኛ/ በአካባቢው ቤተክርስቲያን አ
ለመኖርና ያለውም በ፲ ኪሎ ሜትር ር
ቀት ላይ በመሆኑ ካህናት ሥርዓተ ቤተ
ክርስቲያንን ከሌላው ትምህርት ጋር ለማ
ጥናት ያስከተለው ችግር ከፍ ያለ ሆኖ
በመገኘቱ ሥራውን በዚህ ቦታ ላይ መ
ቀጠሉ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመ
ዝን ሆኖ ተገኝቷል ስለዚህም ብፁዕነታ
ቸው ጉዳዩን ከሚመለከታቸው ጋር ተ
ነጋግሮ ማሰልጠኛውን ወደ መንበረ
ሊቀ ጵጵስናው የሚዛወርበትን እርምጃ
መውሰዱ የመጀመሪያው ሥራቸው አ
ደረጉት ።

ጥረቱ ቀጥሎ የክፍለ ሀገሩ አስተዳደ
ር መ/ቤት ለቀረበለት የቦታ ለውጥ ጥ
ያቄ ወዲያውኑ መልስ አግኝቶ በየደረ
ጃው ላሉት የአስተዳደር ዘርፍ መ/ቤቶ
ች ትዕዛዝ ተሰጥቶ በወረዳና ቀበሌ በገ
በሬ ማኅበራት በኩል በተደረገው ትብ
ብር ለማሰልጠኛው በቂ የሆነ ቦታ በ
ሕጋዊ ሠነድ የሀገረ ስብከቱ ተወካዮች
እንዲረከቡት ተደረገ ። ብፁዕነታቸው
የልማቱ ሥራ ወቅቱ ሳይተላለፍ በአስ
ቸኳይ እንዲቀጥል በማድረግ በቡናና
ሻይ ተክል ማሻሻያ የድርጅቱ ኃላፊዎች
ና የልማት ባለሙያዎች ትብብር ፰፻
ችግኝ ቡና የቡናን በሽታ መከላከል የ
ሚችል የዘመናዊ አሠራር ተተከለ ። በ
ዚህ የልማት ሥራ ላይ የሀገረ ስብከቱና
የማሠልጠኛው ት/ቤት ሠራተኞች እን
ዲሁም በመቱ ከተማ በ፫ቱ አድባራት
የሚገኙ ካህናትና ምዕመናን የጉልበት
አስተዋጽኦ አድርገዋል ። ምንም በተሰ
ጠው አዲስ ቦታ ላይ የሚደረገው የልማ
ት እንቅስቃሴ ቢቀጥልም በማሰልጠኛ
ው ዝውውር በላይ አካል ለማስፈቀድ
አስፈላጊ በመሆኑ ብፁዕነታቸው የቦ
ታውዝውውርያስፈለገበትንምክንያት
በዝርዝርገልጸውሪፖርትለብፁዕወቅ
ዱስአቡነተክለሃይማኖትርዕሰሊቃነጳ
ጳሳትወፓትርያርክዘኢትዮጵያበማቅረ
ብ ቅዱስነታቸው ለቤተ ክርስቲያን እ
ድገትና እርምጃ መፋጠን ባላቸው ሙ
ሉ ፍላጐትና ብልህ አመራር ወዲያውኑ
አንድ የልዑካን ቡድን በቦታው ደርሶ
እንዲያጠናው መመሪያ ትዕዛዝ በመስ
ጠት በብፁዕ አቡነ ገሪማ በምድረ ሱዳ
ን የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ የኢትዮጵያ አ/
ተ/ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ልማ
ትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ተ/ዋና ጸሐ
ፊ የሚመራ ሊቀ ህሩያን መርሐ ጽድቅ
ገ/ሕይወት በጠቅላይ ቤተ ክህነት የስብ
ከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መም
ሪያ ኃላፊና የመንበረ ፓትርያርክ አጠ
ቃላይ ሰበካ አስተዳደር ሥራ አስፈጻሚ
ኮሚቴ አባል ሊቀ ካህናት ጥዑመ ልሳ
ን ካሣ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የትምህር
ትና ማሠልጠኛ መምሪያ ኃላፊ አቶ ዘ
መድኩን ብዙወርቅ በኢ.ት/ኦር/ተ/ቤተ
ክርስቲያን ልማትና ክርስቲያናዊ ተራ
ድኦ መምሪያ የፕሮግራሞች አስተባባ
ሪና የእቅድና የሥራ አመራር አማካሪ
በአባልነት የሚገኙበት ቡድን ወደ ኢ
ሉባቦር በመምጣት ቀደም ሲል ማሰል
ጠኛው የነበረበትን ቦታና አሁን አዲ
ስ ለማሰልጠኛው ከመንግሥት የተሰጠ
ውን ቦታ አንድ በአንድ በማጥናትና ከ
ሚመለከታቸው ጋር የጋራ ጥናታዊ ው
ይይት በማድረግ ተመልሰው ለቅዱስነ
ታቸው ባቀረቡት ሪፖርት መሠረት ቅ
ዱስነታቸው መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ
ማሰልጠኛው ከነበረበት ወደ መቱ ከ
ተማ ተዛውሮ ሥራውን እንዲቀጥል ፈ
ቅደው በልማትና ተራድኦ መምሪያ በ
ኩል የዝውውሩ ፈቃድ እንደደረሰን በ
ቅደም ተከተል ሊከናወኑ የሚገባቸው
ማለት የቤት ሥራ የንብረት መጓጓዝ ለ
፲ኛ ዙር ኮርስ ቅድመ ዝግጅት የማድረ
ጉ ሥራ ተጀመረ ።

በዚህም መሠረት ፣

፩ኛ/ ለቤት ሥራ የተፈቀደ በጀት ባይኖ
ርም ለማሰልጠኛው ሥራ ማስፈጸሚያ
የተፈቀደውን በጀት በማብቃቃትና በ
ልማት ከተገኘው ገቢ አሥር ክፍል ቤ
ቶች በአዲሱ ቦታ ላይ በአጣዳፊ ሁኔታ
በመሥራት ፣

፪ኛ/ በዳበና የነበሩትን ንብረቶችን
ማጓጓዝ ከፍተኛ ወጭ በመጠየቁ የክፍ
ለ ሀገሩ አብዮታዊ ፖሊስና የመንገድ
ሥራ ድርጅት የመኪና እርዳታ በብፁዕ
ነታቸው ተጠይቆ በሁለቱ መ/ቤቶች
ትብብር ከፊል ንብረቶችና ዕቃዎችን በ
ማጓጓዝ ፣

፫ኛ/ ለ፲ኛ ዙር ኮርስ አስፈላጊውን
ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ፣

፬ኛ/ የልማቱን ሥራ ማለትም የቡና
ው ልማትም ሆነ በጐኑ የሚካሄደውን
የጓሮ አትክልት ቦታ የማዘጋጀት ሥራ
በቅደም ተከተል ተከናውኖ የማሠልጠ
ኑን ፕሮግራም ከጥቅምት ፲፱፻፸፯ ዓ.
ም ለመጀመር ተቻለ ።

ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ የክፍለ ሀገሩ
ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ፀሐፊ
በዚህ ማሠልጠኛ ት/ቤት በማስተማር
የማሰልጠኛውም የልማት ሥራ ዕለት
በዕለት ከቦታው ባለመለየት በማስተባ
በር በመቆጣጠርና በማበረታታት ሥ
ራው አሁን ከሚገኝበት ደረጃ ላይ እን
ዲደርስ ያደረጉት ጥረት በቀላሉ የሚገ
መት አይደለም ።




www.ethiopianorthodox.org

# መድኃኔ ዓለም

በዘመናችን የተሟላ ጤንነት ያለውን ሰው ማግኘት ያዳግታል ። በመሆኑም አብዛኛው በተለያዩ መንገዶች መድኃኒት ፈላጊ ነው ። ለሚሻውም ሕመምተኛ በተለያየ የዕውቀትደረጃ መድኃኒቶች ይቀመማሉ ስለሆነም በዓለም ላይ እጅግ ብዙ ዓይነት መድኃኒቶች ይገኛሉ መድኃኒቶች እንደ ዓይነታቸው መብዛት ግልጋሎታቸውም እንዲሁ ይለያያል አንዱ ከሌላው የተሻለ የመፈወስ ኃይል ይኖረዋል ቢሆንም መድኃኒቱ ሁሉ ፍቱን ነው ማለት አይደለም ምክንያቱም ከባህላዊ መድኃኒት እስከ ፋርማሲስቱ ቀማሚ በተለያየ መሣሪያና የዕውቀት ደረጃ ስለሚዘጋጅ ነው ስለዚህ በየትኛውም ጥበብና ዕውቀት የሚዘጋጁ የዓለም መድኃኒቶች የሚሰጡት ፈውስ ሥጋ ፍጹም አይደለም ።

መድኃኔ ዓለም የሚለው መጠሪያ ለሰው ልጅ ሁሉ የነፍስ የሥጋ መድኃኒት እንዲሆን ለመጣው ለእግዚአብሔር አንድያ ልጅ የተሰጠ ስም ነው ። መድኃኔ ዓለም ማለትም የዓለም መድኃኒት የዓለም መድኅን ማለት ነው ። ይህ ስም ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍቅር የተነሣ ሥጋ ለብሶ ስለኃጢአተኞች ለተሠዋው መድኅን ክርስቶስ የፍጹም አዳኝነቱ መጠሪያ ነው ። ወልደ እግዚአብሔር በሥጋ ሲገለጥ የተለያዩ ስምን ተሰጥተውታል ። መሢሕ (ክርስቶስ) አምላክ ወሰብእ ስለመሆኑ ፣ አማኑኤል ሥጋ ለብሶ ከእኛ ጋር አንድ ስለመሆኑ ኢየሱስ እኛን ከፍዳ ኃጢአት ለማዳኑ የተሰጡት ስሞች ናቸው ። ከእነዚህ ስሞች በተለይ "ኢየሱስ" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል አስቀድሞ በመልአኩ እንደተነገረው ክርስቶስ ሲወለድ



ክርስቶስ በመስቀሉ እኛን ከፍዳ አዳነን

የወጣለት የተጸውዖ ስሙ ነው ። ትርጉሙም ፦ መድኃኒት ፣ መድኅን ፣ አዳኝ ማለት ነው ። "እነሆም ፣ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ" (ሉቃ. ፩፥፴፩) "…. ልጅም ትወልዳለች ። እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ"(ማቴ. ፩ ፣ ፳፩)። ከዚህ በቅዱስ መጽሐፍ ከተገለጠው የአዳኝነቱ ስም በመነሣት የኢትዮጵያ ምእመናን በራሳችን ቋንቋ መድኃኔ ዓለም ብለውታል ። ይህ በትክክል የተሰጠ አጠራር ነው ።

መድኃኔ ዓለም መባል የተገባው በነፍስ በሥጋ ሊያድን የቻለው የእግዚአብሔር ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው ።

መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በራሱ መሥዋዕትነት ዓለምን ያዳነው እንደ ውኃ ፈሳሽ ፣ እንደ እንግዳ ደራሽ ፣ እንዲሁ በድንገት አይደለም ፣ ቀደም ሲል እግዚአብሔር በኃጢአት ለወደቀው አዳም በሰጠው ተስፋ መሠረት ነው እንጂ (ዘፍ.፫፥፲፭) ። ሰው ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ ከአምላክ ጸጋና ከሚኖርበት ተድላ ደስታ ውጭ ሆነ ፣ ሞትም ተፈረደበት ፣ ይኸውም ከእግዚአብሔር አንድነት ተለየ ፣ በዲያብሎስ ተንኰልና የማታለል ፍላፃ ተወግቶ ፣ ከፉኛ ቆስሎ በወጥመዱ ተያዘ ሆኖም የተሰጠውን ተስፋ ፍጻሜ ለማየት ከትውልድ ወደ ትውልድ በናፍቆት ሲጠባበቅ ኖረ ። ይልቁንም በየዘመኑ የተነሡት ነቢያት ስለዚህ ተስፋ ትንቢት በመናገር በመንፈስ ብቻ ቃኝተውት አልፈዋል ። "መድኃኒትንም ለሕዝቡ ሰደደ ኪዳኑንም ለዘላለም አዘዘ ስሙ የተቀደሰና የተፈራ ነው ።" መዝ. ፩፻፲፥፱)

"…ስለዚህ የገዛ ክንዱ መድኃኒት አመጣለት ፣ ጽድቅም አገዘው" (ኢሳ. ፶፱፥፲፮) እግዚአብሔር የተናገረውን የሚያደርግ ፣ ቃሉን የሚያጸና ፣ የሰጠውንም ተስፋ የሚፈጽም አምላክ ነውና ፣ "… የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ ፣ … ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ ።" (ገላ. ፬፥፬) ። በሰው ሥጋ ያደረው የኃጢአት ደዌ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ በመወለዱ ፍቱን መድኃኒት ተገኘለት ።

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና (ዮሐ. ፫፥፲፮) ። የእግዚአብሔር ፍቅር እጅግ ጥልቅ ነው ፣ ከአእምሮአችን በላይ ነው ። ቅዱስ ጳውሎስ ገና ጠላቶቹ ሳለን ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውን አንድያ የባህርይ ልጁን ለሞት አሳልፎ እስከ መስጠት ደርሶ ወደደን ። እንዲሁም ጳውሎስ ፦ ስለ ጻድቅ ሰው የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና ፣ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ግን ስለ ኃጢአተኞች ሞተ ብሏል። ስለሆነም በእርሱ የሚያምን ሁሉ ለነፍሱ መድኅን አግኝቷል ፣ የዘላለም ሕይወት አለው ፤ ይኸውም እግዚአብሔር ፍቅሩን በገለጠበት ፣ ሕያው መሥዋዕት በሆነው በልጁ ሞት በማመን በኃጢአት ምክንያት ከሚመጣብን ፍርድ እንድንድን ነው ።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የተወደደ መዓዛ ያለው የኃጢአት መሥዋዕት ነው ። እርሱ ኃጢአት የሌለበት ፍጹም አምላክ በመሆኑ የኃጢአትን ዋጋ በደሙ ሊከፍል ችሏል ። ሞቱ በጸዋትወ መከራ የተፈተነ ፣ ከጌቴሴማኒ እስከ ቀራንዮ እጅግ መራራ የመስቀል ጉዞን ያጠቃለለ እንጂ ተራ ሞት አይደለም ። መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ሁሉን በራሱ መሥዋዕትነት ከፈጸመ በኋላ በመስቀል ላይ ሆኖ "ሁሉ ተፈጸመ" ሲል ተናገረ ። "በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል ።" (ዕብ ፲፥፲ አንድ ጊዜ ራሱን በመሠዋት ሁሉን ፈጽሟል ። ይህ ከማስተዋል በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር "ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ያዳነበት ይረቃል" የሚለውን የአበው አባባል ያስታውሰናል ።

የክርስቶስ ሞት በኃጢአት ምክንያት ለተፈረደብን ሞት ምትክ ነው በዕዳ ተይዘን ነበርና ስለነፍሳችን ቤዛ ሆኖ ሞተልን ። ስለዚህ እኛ በነፃ ተለቅቀናል ። ለምሳሌ ፦ በአገራችን እንደሚታወቀው የቤት እንስሳት የሰው ሰብል ቢያበላሹ ባለንብረቱ ደርሶ በዕዳ ይይዛቸዋል የጠፋው ሰብል ዋጋ ሳይከፈል አይለቅቃቸውም ። ሆኖም የእንስሳቱ ባለቤት የተገመተውን ክፍሉ ይወስዳቸዋል ፣ እንስሳቱ ነፃ ይለቀቃሉ ። ይህ ክፍያ አፈ ላማ ይባላል ። እንዲሁም ሰው በስሕተት ነፍስ ቢገድል የገዳይ ወገኖች ተሰብስበው እንደባህሉ የተወሰነውን የደም ዋጋ ("ጉማ" ይባላል) ለሟች ዘመዶች ይከፍላሉ ። ከዚህ በኋላ ገዳዩ ነፃ ይወጣል የሟች ወገኖች በደም አይፈልጉትም ። ይህም ክርስቶስ ላደረገልን ቤዛ መልካም ምሳሌ ነው ። መድኃኔ ዓለም ስለእኛ ምትክ ሆኖ ከሞት ዕዳ ዋጀን ቤዛ መስጠት ወይም መዋጀት መልሶ መግዛት ማለት ነው ። ጌታ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ተለይተን ለሰይጣን ባርነት ከተሸጥንበት መልሶ በደሙ ገዛን ። (፩ኛ/ጴጥ. ፩፥፲፰-፲፱) ።

ስለዚህ መድኃኔ ዓለም ቤዛችን ነው፤ በራሳችን ልንወጣው ያልቻልነውን የኃጢአት ዕዳ በክቡር ደሙ ከፍሎልናልና ። ዛሬ በእርሱ ያመንንና ተስፋ ያደረግን ሁላችን በኃጢአት ምክንያት ከሚመጣው የፍርድ ቁጣ እንድናለን ። በመድኃኔ ዓለም ንጹሕ ደም ታጥበን ከነፃን ወዲያ እንደገና በኃጢአት መያዝ አይገባንም (ቲቶ ፪፥፲፩-፲፩ ዕብ. ፲፥፳፯-፳፯)።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በየዓመቱ መጋቢት ፳፯ ቀን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ስለ እኛ በመስቀል መሰዋት በማሰብ መድኃኔ ዓለም በተሰኘው ስያሜ በዓሉን ታከብራለች ።

ተስፋዬ ረጋሣ

ይህ ማሰልጠኛ እስካሁን ፕሮግራሙን የሚያካሂደው በጊዜያዊ ቤቶች በመሆኑ በቂ ቤት የሚያገኝበት ወይም ለቤት መሥሪያ ገንዘብ ለማግኘት ገና ብዙ ጥረትና የበላይ መ/ ቤት ትኩረትን ይጠይቃል ።

ሊቀ ትጉሃን ብርሃኑ መንገሻ





www.ethiopianorthodox.org

# የጤና ዓምድ

## የሳንባ ነቀርሳ በሽታ

የሳንባ ነቀርሳ በሽታ የዘር የጾታና የእድሜ ልዩነት ሳያደርግ ማንንም ሰው ሊይዝ የሚችል አደገኛና አሰቃቂ የሆነ ተላላፊ የሕብረተሰብ በሽታ ነው ፣ ይህ በሽታ በየትኛውም ሀገር በተለይም ባልሠለጠኑና የኑሮ ደረጃቸው በጣም ዝቅተኛ በሆኑት አገሮች የሚገኝ ነው ።

ይህ በሽታ የማንኛውንም የሰውነት ክፍል ሊይዝ ሲችል በተለይ ሳንባን የማጥቃት ጠባይ ስላለው የሳንባ ነቀርሳ በሽታ ተብሏል ።

በሽታው በተለይ ከ፲፭ ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑትንና ለበሽታው መከላከያ ክትባት ያላገኙትን ልጆች በይበልጥ ያጠቃቸዋል ።

የሳንባ ነቀርሳ በሽታ የሚመጣው በዓይን በማይታዩ እጅግ ረቂቅ በሆኑ ሕዋሳት ነው ሕዋሳቱ ሊታዩ የሚችሉት ማይክሮስኮፕ በሚባል አጉልቶ በሚያሳይ መነጽር ብቻ ነው ።

### የበሽታው መተላለፊያ መንገዶች

፩ኛ/ ሕመምተኛው በሚስልበት ጊዜ በሽታውን ሊያመጡ የሚችሉትን ረቂቅ ነፍሳት ከአፍ ከሚመጡት ነጠብጣቦች ጋር አየር ውስጥ ይረጫል በዚህን ጊዜ በአካባቢው ያለው አየር በሕዋሳቱ ይበከላል በአቅራቢያው ያለ ጤነኛ ሰው ይህን አየር ወደ ውስጥ በመተንፈስ ወደ አካሉ ሲያስገባው ሕዋሳቱም ወደ ውስጥ ከተነፈሰው አየር ጋር አብረው ይገባሉ ። በሽተኛው በሚስልበትና በሚያነጥስበት ጊዜ የሳንባ ነቀርሳ ሕዋሳት ከአፉ ከሚወጡ ነጠብጣቦች ጋር አብረው ይወጣሉ ጤነኛው ሰው ነጠብጣቦችን ከአየር ወደ ውስጥ ከተነፈሰ በበሽታው ይያዛል ።

፪ኛ/ ሕመምተኛው ሰው አክታውን በየቦታው ሲተፋ አክታው በወደቀበት ሥፍራ ይደርቃል የሳንባ ነቀርሳን ሊያመጡ የሚችሉ ሕዋሳቶች ከሕመምተኛው አክታ ጋር ስለሚወጡ የደረቀው አክታ ለዚህ በሽታ መምጣት ምክንያት የሚሆኑትን ሕዋሳት እንደተሸከመ በነፋስ አማካይነት ከወደቀበት ቦታ እየበነነ አየር ውስጥ ይገባል ይህን አየር በአጋጣሚ ወደ ውስጥ የተነፈሰ ሰው ሕዋሳቱን ወደ አካሉ ሊያስገባና በበሽታው ሊመረዝ ይችላል ።

የሳንባ ነቀርሳ የያዘው ሰው አክታውን በየሥፍራው ከተፋ ጤነኛ ሰዎችን በበሽታው ሊበክል ይችላል ።

፫ኛ/ በነቀርሳ በሽታ በተያዙ ላሞች የሚገኘው ወተት በሳንባ ነቀርሳ ሕዋሳት የተበከለ ነው ይህ ወተት በደንብ ሳይፈላ ጥሬውን የተጠጣ እንደሆነ ሕዋሳቱ ሳይሞቱ ወደ ጠጣው ሰው አካል ይገባሉ ።

### ሕመሙ የሚያሳያቸው ምልክቶች ፤

አክታ ያለው ሳል እየደጋገመ ያስላል በሽታው እየቆየና እየጠነከረ ሲሄድ ከአክታው ጋር ደም እየተቀላቀለ ይወጣል ። መጠነኛ ትኩሳት ያሳያል ። ሌሊት በመኝታ ጊዜ ሰውነት በላብ ይጠመቃል ። የምግብ ፍላጐት ይቀንሳል ። ሰውነት እየከሳና እየመነመነ ይሄዳል

አንድ ሰው የሳንባ ነቀርሳ ሕመም እንዳለበት በቶሎ ከታወቀና ሐኪም የሚሰጠውን ትእዛዝ በሚገባ ሳያቋርጥ ከፈጸመ ከሕመሙ ሊድን ይችላል ፣ ሕክምናውን ረዘም ላለ ጊዜ መውሰድ ስላለበት ሕመምተኛው የዳነ ቢመስለውም ሐኪሙ በቃህ ካላለው ሕክምናውን ማቋረጥ የለበትም መድኃኒት በመውሰድ ከሚደረገው ሕክምና ሌላ የመነመነውን ሰውነት ለመጠገን በሽተኛውም ብርታት አግኝቶ ከሕመሙ በቶሎ እንዲፈወስ መጠኑና ዓይነቱ የተስተካከለ ምግብ እንዲያገኝ ያስፈልጋል ። በተለይም ሥጋ ፣ እንቁላል ፣ ዓሣ ፣ ወተትና አይብ ፣ እንዲሁም አትክልትና ፍራፍሬ ጠቃሚ ምግቦች ስለሆኑ በየቅኑ እንኳን ባይሆን አልፎ አልፎ ሊገኙ በሚችልበት ጊዜ መመገብ ከበሽታው በቶሎ ለመዳን ይረዳል ።

### ሕመምተኛው ሰው ሊያደርገው የሚገባው ጥንቃቄ

፩ኛ/ ሕመምተኛው የሚገለገልባቸው ሣህን ብርጭቆ... ወዘተ ለሱ ብቻ እንጂ ሌሎች ሰዎች እንዳይገለገሉባቸው ማድረግ ፤

፪ኛ/ ሕመምተኛው ሲስልና ሲያነጥስ አፉንና አፍንጫውን በመሐረብ መያዝ አለበት ከሰው ፊትም ዘወር ብሎ መሳልና ማነጠስ አለበት ።

፫ኛ/ ሕመምተኛው አክታውን በቆርቆሮ እያጠራቀመ መቅበር ወይንም ማቃጠል አለበት ።

፬ኛ/ ሕክምናውን ያለማቋረጥ ሐኪም ቤቃ እስከሚል ድረስ መከታተልና ስለ በሽታው ከሐኪም የሚሰጠውን ምክር በጥንቃቄ መፈጸም አለበት ።

### የሕመምተኛው ቤተ ሰቦች ሉያደርጉት የሚገባ ጥንቃቄ

፩ኛ/ ከቤተሰብ ውስጥ አንድ ሰው በሳንባ ነቀርሳ ሕመም መያዙ ሲረጋገጥ መላው የቤተሰብ አባላት ወዲያውኑ በአቅራቢያቸው ወደሚገኘው ሕክምና ድርጅት ሄደው መመርመርና ምክር ማግኘት አለባቸው ።

፪ኛ/ በበሽታው አለመያዛቸው በምርመራ ከተረጋገጠ በኋላ ለወደፊቱ እንዳይዛቸው የመከላከያ ክትባት መውሰድ ያስፈልጋቸዋል ። በተለይ በቤተሰቡ ውስጥ ዕድሜያቸው አነስተኛ የሆኑ ሕፃናት ካሉ የመከላከያውን ክትባት በፍጥነት መውሰድ አለባቸው ።

፫ኛ/ ተፋፍጎ መኖር ለዚህ በሽታ መዛመት ዓይነተኛ ምክንያት ስለሆነ በአንድ ክፍል ውስጥ ብዙ ሰዎች ሆነው እንዳይኖሩ በተለይም እንዳይተኙ የመኖሪያ ቤት ክፍሎች ለማበርከት መጣር ይጠቅማል ቤቱም አየርና ፀሐይ እንዲጋባበት ሁለት በሮችና ቢቻልም መስኮቶች እንዲኖሩት ማድረግ ይጠቅማል ፤

፬ኛ/ መላው የቤተሰቡ አባላት ከሕመምተኛው ከሚወጣው አክታ ጋር መነካካት የለበትም ። የሚቻል ከሆነ ከቤተሰብ ውስጥ አንድ ሰው ብቻ የሕመምተኛው ረዳት ሆኖ የቀረው ሰው ከበሽተኛው ጋር ብዙ ግንኙነት ማድረግ የለበትም ።

### ጠቅላላ ኅብረተሰብ ሊያደርገው የሚገባው ጥንቃቄ

፩ኛ/ ኅብረተሰቡ ባጠቃላይ የሳንባ ነቀርሳን አደገኛነትን ተገንዝቦ የመንግሥትና የሌሎች ድርጅቶች ይህን በሽታ ለመከላከል የሚያደርጉት ጥረት መተባበር ፤

፪ኛ/ ሕፃናትን ይህ አደገኛ በሽታ እንዳይዛቸው ማስከተብ ፤

፫ኛ/ በሚስሉበትና በሚያነጥሱበት ጊዜ ከሰው ፊት ዞር የማለትን አፍንና አፍንጫን በመሐረብ የመያዝን አክታን የትም ከመትፋት የመቆጠብን ልማድ ማዘውተር ይህ በሽታ እንዳይስፋፋ ይረዳል ።

፬ኛ/ ባጠቃላይ የግልና የአካባቢን ንፅሕና መጠበቅ በጣም አስፈላጊ ነው።

ከሲ/ር የሽወርቅ ከበደ

# የግብርና በረከት

ግብርና ሲባል ለእርሻ ብቻ የሚአመቹትን ቦታዎች በመንከባከብና በመጠበቅ ማረስ ሳይሆን ሌሎችንም ለእርሻ አመች የማይሆኑትንም ቦታዎች ለከብት ግጦሽ አገልግሎት ለደን ማልሚያ እንዲአገለግሉ እንደእርሻ መሬታችን መንከባከብ ያስፈልጋል ይህም ሲባል ተራራማ ቦታዎች አፈራቸው በውሃ (በጐርፍ) በነፋስ እየታጠበ እንዳይወሰድ እርከን በመሥራት ችግኝ በመትከል መንከባከብ ያስፈልጋል በዛሬውም የግብርና በረከት ጽሑፋችን የምንገልጽላችሁ ስለደንና ዱር አራዊት ጥበቃን የሚመለከት ይሆናል ይህም ጽሑፍ የተገኘው ከግብርና ሚኒስቴር የማስታወቂያና የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ከየካቲት እስከ የካቲት ከሚለው መጽሔት በገጽ ፹፯ ላይ ነው ።

የሀገራችን የተፈጥሮ ሐብቶች ልምላሜ በሚገባ የመጠበቅ የማልማትና በሣይንሣዊ ዘዴ በመንከባከብ የቁጠባ አጠቃቀም ማድረግ አንዱና ዋንኛው ብሔራዊ ግዴታችን ነው ይህም ሲሆን የተፈጥሮ ሚዛን ይጠበቃል ሊደርስ የሚችለው የኢኮኖሚ ውድቀትና የማህበራዊ ኑሮ ቀውስ ይወገዳል ለተከታታይ ትውልድም አኩሪ ቅርስ ሁኖ ይቆያል ይልና መጽሔቱ ፍሬ ነገሩን በማራዘም መንግሥት ይህንን የልማት ዘርፍ ለማልማት ፣ ለመጠበቅ ሥርአት ባለው መንገድ ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲቻል የግብርና ሚኒስቴር በተጠናከረ መልክ እንዲዋቀር ከአደረገ በኋላ የደንና ዱር አራዊት ጥበቃና ልማት ባለሥልጣን እንዲሁም የአፈርና ውኃ ሀብት ልማትና ጥበቃ መምሪያ ከፍተኛ ተግባራዊና ውጤታማ ጥረት በማድረጋቸው መሆኑ አያጠያይቅም ።

እነዚህ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥቤቃ የሥራ ዘርፎች የሚያተኩሩባቸው ዋና ዋናዎቹ ተግባሮች ችግኝ ማፍላት፣ ችግኝ ተከላ ፣ የደን ውስጥ መንገድ ሥራ የደን ከለላ ቅየሣ ፣ እርከን ሥራ ግድብ ሥራ የውሃ ጉድጓድ መቆፈር ክትር ሥራ ምንጭ ማጐልመስ ሥልጠና ኩሬ ቁፋሮ መጋቢ መንገድ መሥራትና መጠገን የዱር አራዊት ጥቤቃ የፓርክ ውስጥ መንገድ የገበሬ ተወካዮች ማስልጠን ፣ የደን ምዝገባና የመሳሰሉት የተፈጥሮ ሐብት መጠበቅ ማልማትና በትክክል ሥራ ላይ ማዋል ሲሆን በነዚህ አኳያ አያሌ ተጨባጭ የሆኑ ሥራዎች ተከናውነዋል ።

እነዚህ የልማት ዘርፎች ሥራቸውን ከጊዜ ወደጊዜ ይበልጥ በማሻሻል ተግባራቸውን ከአይነት ወደጥራት እያሸጋገሩ ከመሄድ ጋር የልማት ሥራው በሕዝባዊ ድርጅቶችም እንዲታቀፍ በማድረግ ላይ ናቸው ጠቅለል ባለ መልክ በዚህ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የልማት ዘርፎች ያከናወኑአቸው የሥራ ውጤቶች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል ።

በአፈርና ውሃ ልማት ጥበቃ ዘርፍ የተከናወኑ ዐበይት ተግባራት እንደሚከተለው ነው ።

ችግኝ ማፍላት በቁጥር ፰፩ሚ.፰፻፵፪ሺ.፱፻፵፩ ፤ ችግኝ ተከላ በቁ. ፹፭ሚ.፪፻፲፭ሺ.፴ ፤

የእርከን ሥራ ኪ.ሜ ፩፻፵፯ሺ.፫፻፯ ከትር ሥራ ኪ.ሜ ፱፻፵፩ ወዘተ እነዚህንና እዚህን የመሳሰሉ ሰፋ ያሉ የሥራ ውጤቶችን በሥራ ተርጉመው እናያለን ።

አገራችን የተፈጥሮ ልምላሜዋ ተጠብቆ ለዜጐቿ ጠቀሜታ የሚውሉትን የተፈጥሮ ሀብት በሥራ ላይ ለማዋል በመጀመሪያ ደረጃ ይህንኑ ሀብት መንከባከብና ማልማት አስፈላጊ በመሆኑ በአፈርና ውሃ ጥበቃና ልማት መምሪያ የተከናወኑ የሥራ ዘርፎች በቀላል የሚገመቱ አይደሉም በተለይም በሐረርና በወሎ ክፍላተ ሀገራት የተሠሩት የእርከን የክትሮችና የችግኝ ተከላ ሥራዎች ከሀገር አቀፍ አልፎ በውጭውም ዓለም ዜና ማሰራጫዎች በአድናቆት ተጠቅሶ ተገልጿል ።

የአፈርና ውሃ ልማትና ጥቤቃ መምሪያ የሚያካሂዳቸው ሥራዎችና የደንና ዱር አራዊት ልማትና ጥቤቃ ባለስልጣን የሚአራምዳቸው የሥራ ዓይነቶች በጠባያቸው ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆን ሁለቱም በአጠቃላይ የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅና ለማልማት የቆሙ የሥራ ክፍሎች ናቸው ።

በሰው ልጅ ሕይወት ላይ አሰቃቂና የዘመናት መከራን ከሚጋብዙት ጉዳዮች አንዱ የደን ሀብትን በሚገባ ካለመጠበቅና ካለማልማት ከሚመጡ መንስኤዎች አንዱ መሆኑ ይታመናል ። እን





www.ethiopianorthodox.org

ዲህ ዓይነቱ ችግር ከሀገራችንም ላይ
እንዳይደርስ ለማድረግ እንዲያስችል
የደንና የዱር አራዊት ልማትና ጥበቃ
ባለሥልጣን የበኩሉን አስተዋጽዖ ያደ
ርጋል ። የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት
ደንን ማልማትና መጠበቅ ብቻ ሳይሆን
በውስጡ የሚኖሩትን እንስሳትና አዕ
ዋፍ የመንከባከብ ኃላፊነትም አለበት
በዚህ የልማት ዘርፍ ከሚከናወኑት ዐበ
ይት ሥራዎች መካከል ከላይ የተጠቀ
ሱት በከፊል ሲሆኑ በተጨማሪም የደን
ውጤቶችን አምርቶ ለሀገር ውስጥና ለ
ውጭ ሀገር ገበያ በማቅረብና በዚህ በኩ
ል የሚአስፈልገውን የሰው ኃይል የማ
ሰልጠን ተግባር ያካሂዳል ።

ስለዚህ ለዚህ ዓይነቱ ከፍተኛ ተግ
ባር የዚህ መምሪያ ብቻ ሳይሆን በዚህ
ጉዳይ ላይ የሚመለከታቸው ክፍሎች
ማለትም የመንግሥትና የሕዝባዊ ድር
ጅቶች ሁሉ የበለጠ ርብርብ ማድረግ
ይፈለግባቸዋል ። ለሀገሬ ተቆርቋሪ ነኝ
ሀገሬን እወዳለሁ የሚል ሁሉ ስለሀገሩ
በሚደረገው ልማትና ሥራ ሁሉ ድጋፍና
ረዳት መሆን ያስፈልገዋል ። ደን ሲጨ
ፈጨፍ ደን ለብሰው የነበሩ ቦታዎች
ባዶአቸውን ሲቀሩ እያየ ዝም ብሎ የ
ሚመለከት ዜጋ ሁሉ የሀገር ተቆርቋሪ
ነኝ ቢል አፍአዊ እንጂ በተግባር ስለአ
ልገለጸው አፍአዊ መውደድ ይሆናል ።
አፍአዊ ወዳጅ ለምንም አይበጅ የተባ
ለው የአባቶች ተረት እንዳይሆን መጠ
ንቀቅ ያስፈልጋልና ።

በዚህም መሠረት ደኖች እንዳይጨ
ፈጨፉ ምድር ምድረ በዳ እንዳትሆን
አንድ ዛፍ ስንቆርጥ ሁለት ችግኝ በመ
ተካት መሆን እንዳለበት ተገንዝበን
ለደን ጥበቃና እንክብካቤ እንሰማራ እ
ላለን ።

ፍሥሐ ባንተ

# እያስተማሩ መማር

እያስተማሩ መማር አሁን የተጀመረ
ሳይሆን ከሐዲስ ኪዳን በፊት የነበረነው
እንደታላቅ ማስረጃ ሊቀርብ የሚችለ
ው የአይሁድ አለቃ የነበረው ኒቆዲሞ
ስ ነው ።

ኒቆዲሞስ የአይሁድ አሊቃ እንደመ
ሆኑ መጠንና በአለበት ኃላፊነት በአን
ድ ወገን አስተዳደሩን የሚመራና በሌላ
በኩል ደግሞ ሕገ አይሁድን የሚአስተ
ምር ታላቅ ሰው እንደነበር ታሪኩ ያስረ
ዳል ።

ቢሆንም እሱ የሚአስተምረው ጥን
ታዊ በመሆኑና ትምህርትን እድሜ አይ
ወስነውም ተብሎ የተነገረውን በመገን
ዘቡ ሕይወት ሰጭ የሆነውን ትምህርት
ለመማርና ለማጥናት ልቡናውን አነሳ
ስቶ በቀጥታ በሥራ ላይ እንዳዋለ እና
ያለን ።

ኒቆዲሞስ እኔ የአይሁድ አሊቃ እና
አስተማሪ ነኝ ብሎ ሳይዝናና ሳይኮራ በ
እርጅና ዘመኑ አዲስ ሕይወት ሰጭ የሆ
ነውን እውቀት ለመማርና ለመቅሰም
እንደተነሳሳ ከዚህ የሚከተለውን እናያ
ለን ።

ኒቆዲሞስ በሚአስተምርበት ዘመን
ትንቢት የተነገረለትና ሱባኤ የተቆጠረ
ለት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ከድንግል ማርያም ተወልዶ እንደ ሕፃ
ናት አድጎ የሐዲስ ኪዳንን ትምህርት
እየተዘዋወረ በሚያስተምርበት ዘመን
ስለነበርና ትምህርቱም አእምሮን የሚ
ያጐለምስ ምድራዊ ጥበብንም ሆነ ሰማ
ያዊ ጥበብን የሚአስገኝ ምድራዊና ሰማ
ያዊ በረከትን የሚያስጥና ግልጽ አድር
ጎ የሚያስረዳ ስለሆነ ቀን ቀን አይሁድ
ን እያስተማረ ማታ ማታ ደግሞ እርሱ
ከክርስቶስ ሲማር እንደነበረ በዮሐንስ
ወንጌል ተጽፏል ኒቆዲሞስ ለክርስቶስ
አንዳንድ ጥያቄዎችን እንደቀረበና
መልሱም በትክክል እንደ ተመለሰለት
በገሀድ ያስረዳል ።

ሙሉ ቃሉም ይህ ነው ። ከፈሪሳው
ያን ወገን የአይሁድ አሊቃ የሆነ ኒቆዲ
ሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ እርሱም
በሌሊት ተነስቶ ወደ ኢየሱስ መጥቶ መ
ምህር ሆይ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር
ከሆነ በስተቀር አንተ የምትደርጋቸው
ን እነዚህን ምልክቶች ሊአደርግ የሚች
ል የለምና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔ
ር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን አለ
ው ኢየሱስም እውነት እውነት እልሀአ
ለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በስተቀ
ር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ
አይችልም አለው ።

ኒቆዲሞስም ሰው ከሸመገለ በኋላ እ
ንዴት ይወለዳል ሁለተኛ ወደ እናቱ ማ
ህፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላል ? እ
ለው ኢየሱስም መለሰ እንዲህ ሲል እ
ውነት እውነት እልሀ እለሁ ሰው ከው
ኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በስተቀር
ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አ
ይችልም ሲል አስረድቶታል ። ዮሐንስ
ምዕራፍ ፫ ቁጥር ፩-፭ ።

ከዚህ ቃል የምንረዳው ነገር አለ እ
ሱም ኒቆዲሞስ ከክርስቶስ እንደ ተማረ
ና እውቀትና መንፈሳዊ ጥበብን እንደ
ተጐናጸፈ ካቀረበው ጥያቄና ክርስቶስ
ም ከሰጠው መልስ ለመረዳት እንችላ
ለን ።

በአንፃሩ ደግሞ እየተማሩ ማስተማር
በኒቆዲሞስና በጌታ ያከተመ ሳይሆን
በቤተ ክርስቲያናችን በኩል ከጥንት
ጀምሮ የነበረና አሁንም ያለ ነው ።

ለምሳሌ ዳዊት የሚማረው ተማሪ
ንባብ የሚማረውን ሲአስተምር ድጓ
የሚማረው ተማሪ ደግሞ ጾመ ድጓ የ
ሚማረውን ተማሪ ያስተምራል እንግዲ
ህ እየተማሩ የማስተማሩ ተግባር አሁን
የተጀመረ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያናች
ን በኩል ጥንታዊነት ያለውና ታሪካዊ
ይዘትም ያለው ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን
ትኩራበታለች ።

አሁንም ቢሆን በመላ ኢትዮጵያ
ድንቁርና ጠፍቶ እውቀት እንዲስፋፋ
በወጣው መርሐ ግብር መሰረት የማስ
ተማሩ ተግባር ከፍተኛው ውጤት እን
ዳስገኘ ሁላችን ምስክሮች ነን ።

እኛም ኒቆዲሞስን መሠረት አድርገ
ን የተነሳነው ነገር ከስሩ ውኃ ከጥሩ
እንደሚባለው ሁሉ ኒቆዲሞስ የእርጅ
ና ዘመኑ ሳይገታው ከክርስቶስ ዘንድ
ማታ ማታ እየሄደ ብዙ እውቀትና ምስ
ጢር እንደገበየ ሁሉ እኛም ቢሆን እር
ጅና ይዘናል የተማርነው ይበቃናል ሳን
ልና ሥራም ቢኖረን እውቀት ወሰን
ስለሌለው ቀን ስንሰራ ውለን ማታ እየ
ተማርን የእውቀት አድማሳችንን ልና
ስፋፋ የምንችል መሆኑን ከኒቆዲሞስ
ልንማር ይገባናል ።

በመሠረቱ አንድ ሰው ካወቀና ከተ
ማረ ራሱንና ሌሎችንም ከስህተት ለማ
ዳን ይችላል ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳው
ሎስም ማወቅና መማር ፣ ተምሮ ማስተ
ማር ጠቃሚ መሆኑን ለጢሞቴዎስ ሲ
አስረዳ እንዲህ ብሏል ።

ይህን እዘዝና አስተምር በቃልና በኑ
ሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም
ለሚአምኑት ምሳሌ ሁን እንጂ ማንም
ታናሽነትህን አይናቀው ። እስከምመጣ
ድረስ ለማንበብና ለመመስከር ለማስተ
ማርም ተጠንቀቅ በትንቢት ከሽማግ
ሌዎች እጅ መጫን ጋር የተሰጠህን በአ
ንተ ያለውን የፀጋ ስጦታ ቸል አትበል።
ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲሆን ይህን
አስብ ፣ ይህንንም አዘውትር ለራስህና
ለትምህርትህ ተጠንቀቅ በእነዚህም ፅና፣
ይህን ብታደርግ ራስህንም የሚሰሙህ
ንም ታድናለህ ብሎታል ። ፩ ጢሞ.. ፬
፲፩-፲፫ ከቅዱስ ጳውሎስ ቃለ ምክር እን
ደምን ረዳው ጢሞቴዎስ በትምህርቱ
እንዲበረታበት በሚአስተምርበት ጊዜ
እንዳይሳሳትና ለሌሎችም መልካም ም
ሳሌ እንዲሆንና ራሱንም ሆነ ሌሎችን
ሊጠቅምና ሊአድን የሚችል መሆኑን
አባታዊ ምክሩን ለግሶለታል ።

ስለዚህ እኛም ቢሆን እየተማርን ከአ
ስተማርን ፩ኛ/ ለራሳችን እውቀትን እን
ገበያለን ፪ኛ/ ራሳችንን ከስህተት እና
ድናለን ፫ኛ/ ሀገራችንንም ሆነ ወገኖ
ቻችንም ስለምንጠቅምበት እያስተማ
ሩ የመማሩን ተግባር እንደ ቀላል ነገር
መቆጠር አይገባንምና ሁላችንም በዚህ
ዓይነቱ ዓላማ መሰለፍ ጠቃሚ መሆ
ኑን ጠንቅቀን እንወቅ ።

ሊ/መ/ ተሰማ ገ/ ሚካኤል



# የሕማማት ሳምንት

ከበዓለ ሆሳዕና ዋዜማ ከቅዳሜ ጀም
ሮ እስከ ቅዳሜ ስዑር ድረስ የሚገኘው
ስምንቱ ቀን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ
ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰሙነ ህማ
ማት ይባላል ። በሌሎች አብያተ ክርስ
ቲያናት ደግሞ ቅዱስ ሳምንት ተብሎ
እንደሚጠራ ይነገራል ። አባባሉ የሚያ
መለክተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ስለ ሰው ልጆች በደል ጸዋተወ መከራ
የተቀበለበት ሳምንት መሆኑን ነው ።
በይበልጥም በቅድስት ቤተ ክርስቲያና
ችን ከቅዱሳን አበው በመጣው ትው
ፊት መሠረት ግብረ ህማማት የተባለው
መጽሐፍ ከሰማኒያ አንዱ ቅዱሳት መጻ
ሕፍት የተውጣጡ ስለክርስቶስ ህማምና
ሞት ስለፈጸመው ርህራሄና መልካም
አገልግሎት በጠቅላላው ስለ ነገረ መስ
ቀሉ የሚናገሩት የተጻፉበት መድበል
ስለሆነ እንዲሁም ነቢያት የተነበዩትን
ሊቃውንት የደረሱትን በወንጌል የተጻ
ፈውን የያዘ ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን
ሲነበብ ይሰነብታል ሕዝቡም እየተሰበ
ሰበ ንባቡን በመስማት የጸሎቱና የስግ
ደቱ ተካፋይ ሆኖ ይሰነብታል ።

በተለይም አማኝ የሆነ ሁሉ በዚሁ
የሕማማት ሳምንት ራሱን ዝቅ የሚያደ
ርግበት መንፈሳዊ አቋሙን የሚያስተ
ካክልበት ህሊናውን የሚመረምርበት
ኃጢአቱን ተናዞ እያዘነ የሚያቃልል
በት ካሮጌ ሕይወቱ የሚላቀቅበት ፣ ከኃ
ጢአት ወደ ጽድቅ የሚሸጋገርበት በጠ
ቅላላው ወደ አዲስ ህይወት የሚለወጥ
በት ቅዱስ ሳምንት ስለሆነ የዝግጅት
ሳምንት ነው ፤ ዝግጅትም ሲባል ራስን
ማዘጋጀት አለ ፣ ሌላውን ማዘጋጀትም
አለ ፤ ይህ የህማማት ሳምንት ግን ራስን
ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን ሌላውንም ማገ
ልገል ማዘጋጀት ያስፈልጋል ፤ ይህም
ማለት ሰብአዊ ርህራሄ የሚፈጸምበት
ና መልካም አገልግሎት የሚሰጥበት
ቅዱስ ሳምንት ስለሆነ ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እየተዘዋ
ወረ ቅዱስ ተግባሩን በሚያከናውንበት
ጊዜ ከማንኛውም ሥራ ሁሉ አገልግ
ሎት የሚበልጥ መሆኑን ለደቀ መዛሙ
ርቱ "የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱን
ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለ
ግሎት አልመጣም" ሲል ገልጾላቸ
ዋል ። ማቴዎስ ፳፥፳፰ ።

ይህን የሰጠውን ተስፋ በተግባር ገል
ጾ ለማሳየት አሁን ቢያዝነው በህማማት
ሳምንት የመጨረሻ አገልግሎቱን ሊሰ
ጥ ራሱን አዘጋጀ በዚህ ሳምንት ለጠቅ
ላላው ህብረተሰብ የፈጸመው ውለታ
ቁጥር የለውም ለየአንዳንዱ ኃጢአተኛ
ሁሉ ሊያገለግል እሽከርና ሎሌ ሆኖ
ቀረበ ።

ለምሳሌ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ያለ አን
ድ ትልቅ ባለስልጣን በመንገድ ዳር የ
ወደቀውን ድሃ ሌላ ሰው እዞ ሳይሆን
እራሱ ከወደቀበት አንስቶ ቁስሉን እያ
ጠበ ቢያስታምመው ያደፈ ሰውነቱን
ም ዕዳት ቢያደርግለት በጠቅላላው ምስ
ኪኑ የሚሰራውን ተግባር ሁሉ ቢያከና
ውንለት አድራጐቱን የሰማና ያየ ሁሉ
እጅግ እንደሚያመሰግነው አይጠረጠ
ርም ሆኖም ይህን መሳዩን አገልግሎት
ውርደት መስሎ ስለሚታየውና በሚያ
ውቁትም ዘንድ ያስነቅፈኛል ብሎ ስለ
ሚገምት በሁኔታውም ስለማይደሰትበት
አይፈጽመውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ግን በዕለተ አርብ መስቀሉን ተሸ
ክሞ ወደቀራንዮ መከራ ጉዞ ተጓዘ ።
በጉዞውም ላይ ዓለምን በኃጢአት ተጐ
ሳቁሎ አገኘው እሱም ድኃና ሐብታም
ሳይል እያንዳንዳችንን ሊያገለግል ስለ
መጣ በደሙ ቁስላችንን አጠበልን ፤ ከ
ዚህም የተነሣ ክርስቶስ አገልጋያችን
ሆነልን የሚለው አነጋገር ለሕዝብ የተ
ሰጠ መልካም በረከት መሆኑን በየጊ
ዜው ልናስታውሰው ይገባናል ።

ምክንያቱም የዓለምን በደልና ጉስ



www.ethiopianorthodox.org

ቁልና በተሸከመበት ወቅት ደዌያችንን በእውነት ተቀበለ ሕማማችንን ወሰደ ስለመተላለፋችንም ቆስለ ስለበደላችንም ደቀቀ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን "በማለት ነቢዩ ኢሳይያስ መስክሯል ። ኢሳ. ፶፫፡ ፬-፭ ።"

በዚህ አኳኋን ሥቃያችንን ሁሉ ስለ ተሸከመልን መንፈሳዊ ነጻነታችንን አገኘን ጠፍቶ የነበረውንም አዲስ ህይወት ተረከብን ይህንን ቃል በእምነት የሚቀበል ምዕመን ሁሉ የህሊና ሰላምን አግኝቶ ከኃጢአቱ ቁስል ይድናል ፤ ስለዚህም ምዕመናን ሁሉ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በሚያደርጉት የመንፈስ ግንኙነት ሕይወታቸው መለዋወጡን ማሳየት ያለባቸው ለሌላው አገልግሎት በማቅረብ ነው ።

አገልግሎት የፈጸመው ክርስቶስ በኋላዬ ፤ ሊከተለኝ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ ፤ እያለ ዛሬም ለአገልግሎት እኛን ይጠራናል፤ይህ ከሆነ እራስን መካድ ማለት ምን ማለት ነው? ራሳቸውን የካዱ እነማናቸው? ሐብት ፣ እውቀት ፣ ትምህርት ፣ ልዩ ልዩ ችሎታ ያላቸው ይህን ሥራ ሠርተውታልን? እንል ይሆናል ይህም ሰብአዊ ርህራሄን አገልግሎትን፤ መልካም አድራጎትን ስለሚጠይቅ ሁሉንም ይመለከታል እንጂ ያታን አይለይም ይህም ማለት ለመልካም ነገር ሀብትንና እውቀትን ራስንም መስዋዕት ማድረግ ሲባል የተለየና እራሱን የቻለ ተግባር አለው ፤ ይኸውም ሁላችን ሥራ ለመሥራትና ሌላውን ለማገልገል ከሆነ እስዋን የሚል የቆረጠላት ድምፅ እንሰማለን ። ይህም ማለት ሁለመናችንን እንሰጣለን ማለታችን እንድሆን ሊገባን ያስፈልጋል ።

እንዲህ ያለውን ሰብአዊ አገልግሎት በቃል ብቻ እየተናገርን በተግባር ካልፈጸምነው መስቀሉን ተሸክመን በኋላው ተከትለናል እራሳችንን ክደናል ለማለት አንችልም ምክንያቱም እኛ እራሳችን እጥፍ ድርብ እየለበስን ለተራቆተው ካላካፈልን ያማረውን ምግብ እያማረጥን እየበላን ሌላው ቢራብ ቢቸገር ግድ የለሾች ከሆን የጣፈጠውንም መጠጥ እስክንረካ እየጠጣን ሌላው ሲጠማ ዝም ብለን ከተመለከትን መራብስ? መጠማትስ? መራቆትስ ምንድ ነው እንዳሉት እንደ ሦስቱ ሰዎች መሆናችን ነው ።

አንደኛ አንድን ሀብታም የተራበ ድሐ ርቦኛልና ዳቦ ስጠኝ ይለዋል ፤ ሀብታሙም እኔ ረሐብን ፈልጌ አጥቼው ተጨንቄአለሁ አንተ ደግሞ እርቦኛል ትላለህ ምን ያለኸው ዘመናይ ነህ ይልና ምንም ሳይሰጥ አሰናበተው ።

ሁለተኛ የተራቆተ ድሃ እራቁቴን ስለ ሆንኩ ብርድ ሊገለኝ ነውና እባክህ ውራጅህን ጣልልኝ ሲል አንዱን ሰው ይጠይቀዋል ። ዘመናዊውም ሰውዬ እኔ እየወበቀኝ ሙቀቱ አስቸግሮኛል በላብ ታፍኛለሁ ቅዝቃዜ ለመፈለግ ይኸው ሚዳ ለሚዳ ስንከራተት ታየኛለህ አንተ ደግሞ በረደኝ ትላለህ ምነው እኔ እንዳንተ በበረደኝ አንተ ምንኛ ታድለሃል አለና አሰናብተው ።

ሦስተኛ ደግሞ የተጠማ ድሃ ሄደና ተጠምቻለሁና የምጠጣው ስጠኝ ሲል ሰውየውን ለመነው ሰውየውም እኔ ማንኛውንም መጠጥ ብጠጣ አላረካኝ ብሎ በመጨነቅ ላይ ሳለሁ አንተ ተጠማሁ ትላለህ ምነው እኔን እንዳንተ በጠማኝ ሲል እያፌዘ አሰናበተው ይባላል ። እንደተባለውም ይህንን መራራ ተግባር የፈጸሙት እነዚህ ሦስት ሰዎች ብቻ አይደሉም የተፈጸመባቸውም እነዚህ ሦስት ድሆች ብቻ አይደሉም በዕለተ ዓርብ አይሁድ በክርስቶስ ላይ እነዚህን ተግባሮች ፈጽመውበታል ስለ ዓለም ኃጢአት እየተሰቃየና እየተራበ ሳለ አንዳች ምግብ ያቀረበለት የለም ።

ይልቁንም ልብሱን ተካፍለው እራቁቱን ሰቀሉት ኃላፊ አግዳሚውም እራቁቱን ሆኖ እየተመለከተ አዲስ ልብስ ሊሰጠው ይቅርና አሮጌ ልብስ እንኳን ሊሰጠው የፈቀደ አልተገኘም በመስቀል ላይ ሆኖ ተጠማሁ ባለ ጊዜ አንድ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ የሚዘከረው ሰው አልተገኘም ። ያጠጡት ነገር ቢኖር ሆምጣጤ ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የተጠማው ሕይወታችን በጥማት ውስጥ በድርቀት ውስጥ ፤ በኃጢአት በረሐ ውስጥ ስለተቃጠለ በሕይወት ውኃ ሊያረካን ነው ።

እንግዲህ ይህን የመሳሰለውን አድራጎት ያከናወኑት ከላይ የጠቀስናቸው ሦስቱ ሰዎች አይሁድ ብቻ ላይሆኑ ይችላሉ እኔና እናንተም ብንሆን በዛሬና በነገ መካከል ስንፈጽመው እንታይ ይሆናል ። እኔን እንደሚርበኝ ሌላውንም ይርበዋል ፤ እኔንም እንደሚጠማኝ ሌላውንም ይጠማዋል ማለትና መጠማት መራቆት ምን እንደሆነ ማወቅ ያስፈልገናል ። ይህን ካወቅን መስቀሉን ተሸክመን በኋላው ለመከተል ፈቃደኞች እንሆናለን እራሳችንንም መካድ ይሉናል ። ይህንን ካላወቅን ግን መስቀሉን ተሸክመን በኋላው ለመከተል እናፍራለን እራሳችንን ለመውደድ እንጂ እራሳችንን ለመካድ ፈቃደኞች አንሆንም መቀበል እንጂ ለተራቡ መስጠት ይደስ አይለንም ።

ይህ እንዳይሆን በዚህ በሕማማት ሣምንት የክርስቶስን ሕማሙንና ስቅለቱን ሞቱንም እያሰብን ሌሎችን ማገልገል ይፈለግብናል ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ቅን ሥራ የሚሰሩትንና በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ሰዎችን የሚያገለግሉትን ስለሚወድ እኛም ከመገልገል ይልቅ ማገልገልን እንምረጥ ፤ ለሌላ ዝቅተኛ ሆና የሚያገለግል እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ትልቅ ነውና ።

አሊቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

---



# ሆሣዕና በአርያም

ይህ ቃል የተነገረ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በሥጋ ተገልጦ እየተዘዋወረ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ወንጌልን ካስተማረ በኋላ ነው ።

ጊዜው ሲደርስ የተነገረውን ትንቢት ለመፈጸም ማለት ለቤዛ ዓለም እንዲሰቀልና እንዲሞት በሞቱም ዓለሙን እንዲአድን ቀደም ብሎ ስለ አስረዳ ። የመስቀል ጉዞውን ወደኢየሩሳሌም ባቀና ጊዜ ሕፃናቱና ሽማግሌዎች ድንጋዮችም ሳይቀሩ ሆሣዕና በአርያም እያሉ አመስግነውታል ።

ይህንም ቃል አራቱም ወንጌላውያን ጽፈውት ይገኛል ። ሆሣዕና በአርያም ማለትም በሰማይ ያለ መድኃኒት ማለት ነው ።

እንግዲህ ከሰማይ በታች በዚህ ዓለም ብዙ ዓይነት መድኃኒት አለ ይህም በጥበበኞች ሰዎች ተመርምሮና ተቀምሞ ሕመምተኞች ሰዎች ይረዱበታል ።

በሽተኞችም ጊዜአዊ ድህነትን ያገኙበታል ። ግን ከብዙዎች ጥቂቶች ቢፈወሱም በአጠቃላይ ሕመምተኞች ሁሉ ሊፈወሱበት አይችሉም የባለ መድኃኒቱም ሥጋዊ ጥበብ የፀጋ ነውና ።

በሰማይ ያለ የኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒትነት ግን እንደዚህ ዓለም መድኃኒት አይደለም ። የእሱ አዳኝነቱ የባህርይ ስለሆነ በጽኑዕ ደዌ ኃጢአት የተያዙትን ሁሉ ፈጽሞ አድኖአቸዋል ።

እንግዲህ የክርስቶስን አዳኝነት አምኖበት ከቀረበ የአልዳኝና የማይድን ከቶ አይኖርምና ከእሱም የተገኘ ሕይወት ዘለዓለማዊ እንደሆነ ተገልጦአል ። ለክርስቶስ አዳኝነት ተመሳሳይ አይኖረውም ጊዜም አይወስነውም ።

በሌላ በኩልም የተአመሙት ሰዎች መድኃኒትን ይፈልጋሉ እንጂ መድኃኒት የተአመሙትን አይፈልጋቸውም ።

ሰማያዊ መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እሱ መድኃኒት ሲሆን አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን በደዌ ነፍስ ተይዘው የተጨነቁትን ራሱ ፈልጎ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ አድኖአቸዋልና ።

ሰማያዊ መድኃኒት ክርስቶስ ከምድራዊ መድኃኒት ልዩነት እንዳለው እንገነዘባለን ።

በመስዋዕትነትም አንፃር ብንወስደው በብሉይ ኪዳን የነበሩ ሊቃነ ካህናት ስለ ድህነት ብዙዎችን በጎችንና ላሞችን በየጊዜው ይሰው እንደነበረ ይተረካል ለጊዜው መስዋታቸው ከአባር ከቸነፈር ቢከላከልላቸውም በደመ እንስሳ መሥዋዕትነት የዓለም ሕይወት ሊድን አልቻለም ነበር ።

ግን ለቀደመ ሰው አዳም በሰጠው ቃል ኪዳን መሠረት ጊዜው ሲደርስ መጥምቁ ዮሐንስ የሕዝቡን ኃጢአት የሚአስተሰርይ የእግዚአብሔር በግ እነሆ ብሎ እንደመሠከረለት መለኮት በተዋሀደው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ዓለም በምልዑ ከደዌ ኃጢአት ተፈውሶ የነፍስ ነፃነትን ተጎናጽፎአል ።

ስለዚህ አብረውት የነበሩ ደቀመዛሙርቱና አዕሩግ ሕፃናት ዓለምን ለማዳን እንደመጣ ቀደም አድርጎ ገልጾላቸው ሆሣዕና በአርያም እያሉ አመስግነውታል ።

አዳኝነቱ እግናዊ መድኃኒት ስለሆነ እየደጋገሙ አመስግነውታል ። በዚያም ጊዜ ገና በአእምሮ ላልጐለመሱ ሕፃናት አምላካዊ ጌትነቱን ገልጦላቸው የእስራኤል ገዢና ፈጣሪ አንተ ነህ እያሉ አመሰግነውታል ።

ዘንባባም ይዘው እንደ ነበረ ተገልጾአል የዘንባባ ዝንጣፊ ይዞ ማመስገንም በእነሱ የተጀመረ ሳይሆን የቀደሙ ሰዎች የደስታ መግለጫ ያደርጉት እንደ ነበረ ይተረካል ።

አብርሃም ይስሐቅን በወለደ ጊዜ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዞ እግዚአብሔርን እንደ አመሰገነ ተገልጧል ።

ያንን መሠረት በማድረግ በዕለተ ሆሣዕና አዕሩግ ሕፃናት የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው አመስግነውታል ።

ዮዲትም ሆሎፎርኒስን ድል በአደረገች ጊዜ እንደዚሁ ዘንባባ ይዛ እንደ አ[illegible]ች ይነገራል ።

[illegible] ብረ ዘይትም በሚአወርደው መንገድ በደረሱ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ደስ ብሎአቸው እግዚአብሔርን አመስግነውታል ። በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ እሱ የተመሰገነ ነው የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው ። እያሉ ባመሰገኑ ጊዜ ፈሪሳውያን ሰምተው መምህር ሆይ ዝም ይሉ ዘንድ ደቀመዛሙርትህን ተቆጣቸው አሉት ።

እነሱም እንዲህ ለማለት የቻሉት እግዚአብሔርን ሲአመሰግኑ ሰምተው በሰይጣናዊ ቅናትና ምቀኝነት ተነሣሥተው ስለነበረ ነው ። የተአምራት ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ፈሪሳውያን በቅናት እንደተነሣሡ አይቶ አስደናቂ ተአምራቱን ለመግለጥ ስለ ፈቀደ ።

እነሱ ዝም ቢሉ እነዚህ ድንጋዮች ያመሰግኑኛል ብሎ አምላካዊ ትንቢቱን አስቀድሞ ገልጦአል ። ሉቃስ ፲፱ ቁጥር ፵ እንግዲህ የእግዚአብሔር የባህርይ ጥበቡ እጅግ የረቀቀና አስደናቂ እንደ መሆኑ ሰዎች እሱን ከማመስገን ዝም ባሉ ጊዜ በሰዎች ምትክ ለዚህ ደረጃ ይበቃሉ ተብሎ ግምት ያልተጣለባቸውንና ሰብአዊ ንባብ፣ አእምሮ የሌላቸውን ድንጋዮችን እንዲአመሰግኑ አስነሥቶአል ።

እንግዲህ ሁሉም በእግዚአብሔር ቃል ስለሚወሰን እነዚህ ድንጋዮች ያመሰግኑኛል ያለው አምላካዊ ቃሉ ድንጋዮችን እንዲአመሰግኑ ወደ ሐዋርያነት መርጦአቸዋል ።

ይህም የባህርይ ሥልጣኑን ለመግለጽ ነው ። አዋቆች ነን የሚሉ ፈሪሳውያን እንዳያውቁ ያላዋቆች አዕባን እንዲአውቁና እንዲአመሰግኑ ማድረጉ ብዙ ትምህርት ይሰጠናል ።

በሌላ በኩልም አዕባን እንደ አመሰገኑ ሲአስረዳ እንዲህ የሚል ንባብ ይገኛል ። ወተደመረ ቃለ ሕፃናት ወቃለ አዕባን ምስለ ስብሐተ መላዕክት ብሎ



www.ethiopianorthodox.org

# ታማኙ አገልጋይ

ታማኝ አገልጋይ ማለት በልዩ ልዩ መከራ ተፈትኖ ፈተናውን በማሸነፍ ለተሠጠው ሥራና ለተጣለበት ኃላፊነት ብቁ ሆኖ መገኘት ነው ።

ከዚህ ሌላ ሰው የሚደሰትበትን ሀገር የሚበለጽግበትን ራሱም የሚጠቀምበትን ሥራ ያለመሰልቸትና ያለስንፍና

---

ከመላእክት ምሥጋና ጋር አንፃዕርአቸው ይገኛል ። የምስጋናውም ቃል ከዳዊት ወገን በሥጋ ለተወለደ መድኃኒት መባል ይገባዋል ።

በሰማይ ያለ መድኃኒት የሚል ነበረ ከዚህም ሌላ በእግዚአብሔር የተፈጠረ ፍጥረት ሁሉ ከፈጣሪው ከተአዘዘ ሁሉም ስለ እግዚአብሔር እንደመሰከረ እንገነዘባለን ። ከእግዚአብሔር ያልተገኘ የለምና ።

በአንድ በኩልም በትንቢተ ዘካርያስ በምዕራፍ ፱ ቁጥር ፱ እንዲህ የሚል ይገኛል የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ እልል በይ እነሆ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነውትሁትም ሆኖ በአህያዪቱ ውርንጫ ተቀምጦ ወደ አንች ይመጣል በማለት ተናግሮአል ።

እንግዲህ ለልዕልናው ተመሳሳይ የሌለውና በዘባን ኪሩብ ሆኖ ሲመሰገን የሚኖር ልዑለ ባህርይ አምላክ ስለ ትሕትናው በዘባነ አድግ ሆኖ ቤተ መቅደስን እንደዞረ ተገልጦአል ።

ክርስቶስ ወደ ዓለም የመጣ በትሕትና እንደ ሆነና ትሕትናንም እንደ መሠረተ ተመልክተናል ።

ከትሕትና የበለጠ ትሩፋት ስለማይኖር እኛም በፍጹም ትህትና ጸንተን እግዚአብሔርን እናገልግለው ።

መምህር ኪዳነ ማርያም አየለ

በንቃትና በትጋት የሠራ እንደሆነ ታማኝ አገልጋይ የሚለውን የማብር ቅጥል ሊያገኝ ይችላል ።

አባቶች "ጠጅ በብርሌ ነገር በምሳሌ" እያሉ እንደሚናገሩት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሳሌ ካስተማራቸው ትምህርቶች መካከል ማቴዎስ ፳፭ ፲፬-፴ ያለውን እንመልከት ለአንድ ሰው ሦስት አገልጋዮች ነበሩት ወደ ሩቅ ሀገር ለመሄድ በተነሣ ጊዜ ሦስቱን አገልጋዮች ጠርቶ ለአንዱ አምስት ለአንዱ ሁለት ለአንዱ አንድ ብር ሰጠና ወጥታችሁ ወርዳችሁ አትርፉበት ብሎ ወደሩቅ ሀገር ሄደ አምስት ብር የተቀበለው አገልጋይ ወዲያው በፍጥነት ጊዜውን በስንፍና ሳያባክን በታማኝነት ወጥቶ ወርዶ በመነገድ አምስት ብር አተረፈና አሥር አደረገ ። ባለ ሁለቱም ብር ነግዶ በማትረፍ አራት አድርጎ አስቀመጠ ባለአንድ ብር ግን እምነት በማጉደል ጊዜ በማባከን ሳይነግድ አንዱን ብር መሬት ቆፍሮ ቀብሮ አስቀመጠው ከጊዜ በኋላ ግን ባለ ቤቱ መጣና ሰዎቹን በመጥራት የሰጣቸውን ገንዘብ ከእነ ትርፉ ተቆጣጠራቸው ።

ባለ አምስቱ ቀርቦ አቤቱ ጌታዬ አምስትብርሰጥተኸኝነበርአምስትአትርፌ አሥር አድርጌአለሁ ብሎ አሥር ብር አስረከበ ፤ ጌታውም አንተ ታማኝ አገልጋይ ነህ በዚህ በጥቂቱ የታመንህ ከሆንህ በቤቱ ሁሉ እሾምሃለሁ አለው ።

ባለ ሁለቱም ብር በትህትና ቀርቦ አቤቱ ጌታዬ ሁለት ብር እንድነግድበት ሰጥተኸኝ ነበረ ወጥቼ ወርጄ በመነገድ ሁለት አትርፌ አራት አድርጌአለሁ ። በማለት አራት ብር አበረከተ ጌታውም ትጉህና ታማኝ ሎሌውን እያመሰገነ በማድነቅ አንተም ታማኝ ሰው ነህ በጥቂቱ ከታመንህ በብዙ ላይ ሹሜህአለሁ አለው ።

በመጨረሻም ሰነፉ ባለአንዱ ብር አገልጋይ መጣና አንዲቱን ብር ይዞ አቤቱ ጌታዬ አንተ ክፉ ጨካኝ ያልሰጠኸውን አንጡ ያልዘራኸውን ሰብስቡ የምትል መሆንህን አውቄ እነግዳለሁ ስል ሌባ ቢሠርቅብኝ ወንበዴ ቢቀማኝና ብከስርምንእከፍላለሁብዬፈርቼጉድጓድ ቆፍሬ ቀብሬያት ነበር ብሎ ራሷን አስረከበው ጌታውም መልሶ አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ ካልዘራሁበት እንዳጭድ ካልበተንኩበትም እንድሰበስብ ታውቃለህን ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበረ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር ብሎታል ።

እንግዲህ ከላይ እንደተጠቀሰው ሠራተኞቹን ጠርቶ የሚሠሩበትና የሚነግዱበት ገንዘብ ሰጥቶ ወደ ሩቅ ሀገር ሄደ የተባለው ባለ ቤቱ የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ታማኝ አገልጋዮች የተባሉ በዚህ ዓለም ያሉ ሕዝቦችን የሚያስተምሩ በሥነ ሥርዓት የሚያስተዳድሩ ኃላፊነት ያላቸው መምህራን ሲሆኑ ትጉሀን የሆኑት ነጋዴዎች በታማኝነት ቀን የፀሐይ ሐሩር የሌሊት ቁር ሳይፈሩ ረኃቡን ፣ የውሀውን ጥም ታግሠው ወጥተው ወርደው በማትረፍ የድካማቸውን ፍሬ አበርክተው ከበረከት ላይ በረከትን ከሹመት ላይ ሹመትን ከክብር ላይ ክብርን አግኝተው ሙሉ ሥልጣን እንደ ተጐናፀፉ ፣ መምህራንም በማስተማር ከሕገ ወንጌል ወጥተው የተሰደዱትንና የባዘኑትን በሕጉ በትእዛዙ መክረው አስተምረው በመመለስና ሰላምን በመፍጠር ደቀ መዛሙርትን በመተካት የምዕመናንን ሕይወት በቃለ እግዚአብሔር በመገንባት ሲደክሙና ሲታገሉ ጊዜያቸውን ጨርሰው ባለ ቤቱ በጠራቸው ጊዜ እድል ፈንታቸው ጽዋ ተርታቸው ከካህናተ ሰማይ ጋር እንደሚሆን መጻሕፍት ይመሰክራሉ ሊቃውንትም በጉባዔ ያስተምራሉ ከመጻሕፍትም ብንጠቅስ በእውነት ለደከሙት ብዙ ደቀ መዛሙርት በማፍራት ጽድቅን እውነትን ሰላምን ለሕዝብ

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል





# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፤

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፤

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዛመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ሰባት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቍ. 110754
የመልእክት ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ ፤

www.ethiopianorthodox.org